12ኛ አመት ቁጥር 14

12th Year No 14

ባህር ዳር ግንቦት 3 ቀን 1999 ዓ.ም

Bahir Dar 11th, May 2007

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

# ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG

## OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA



| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 8.99 Price | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box |



| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| ደንብ ቁጥር 51/1999 ዓ.ም | Regulation No.51/2007 |
| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓት ማስፈፀሚያ ክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ | The Amhara National Regional State Rural Land Administration and Use System Implementation, Council of Regional Government Regulation. |

### ደንብ ቁጥር 51/1999 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓትን ለማስፈፀም የወጣ ክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ

### REGULATION NO.51/2007

A COUNCIL OF REGIOANL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE IMPLEMENTATION OF THE RURLA LAND ADMINISTRATION AND USE SYSTEM IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE

በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ ተፈፃሚነት የሚኖረው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ተሻሽሎ የወጣና በሥራ ላይ እንዲውል የተደረገ በመሆኑ፣

በክልሉ ውስጥ የገጠርን መሬት በይዞታ ለማግኘትና ለመጠቀም የተፈቀደላቸውን አካላት መብትና ግዴታ በማያሻማ ሁኔታ በዝርዝር ህግ በመደንገግ የመሬት አስተዳደር ስርአቱ ፍትሀዊነትን ተከትሎ በሚረጋገጠው የገጠር ልማትና ዕድገት አንፃር የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከድህነት ለመውጣት በሚደረገው ጥረት የማይተካ ድርሻ ያለው በመሆኑ፣

የገጠር መሬት አስተዳደር ስርአቱ በተለይ የሴቶችን፣ የአቅመ ደካሞችንና የወላጅ አልባ ህፃናትን ልዩ ጥቅም ባገናዘበ መንገድ በባለይዞታዎች ሙሉ ተሣትፎ እንዲገነባ ማድረጉ ለተሳለጠ ልማት የላቀ ጠቀሜታ እንደሚኖረው በመታመኑ፤

የመሬቱ ለምነትና የአካባቢው ደህንነት እንዲጠበቅና የመሬት አስተዳደሩ ቀጣይነት ይኖረው ዘንድ በሰፊ የህዝብ ተሣትፎ እንዲታገዝ በማድረግ የመሬት አስተዳደሩና አጠቃቀሙ ግልፅነትን የተላበሰና ተጠያቂነትን የሚያስከትል አሠራር መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በመሬት ይዞታ ላይ የሚፈጠረው የባለቤትነት ስሜት ባለይዞታዎች በክልሉ ውስጥ ጉልበታቸውን፣ ሀብታቸውንና የፈጠራ ችሎታቸውን በማቀናጀት ቀጣይነት ያለው ልማትና የኢንቨስትመንት እድገት በክልሉ ለማረጋገጥ የሚያስችላቸውን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, the Rural Land Administration and use Determination Proclamation to be applicable throughout the Regional State has been Revised and issued to produce an effect.

WHEREAS, The contribution of the land administration system shall, by unequivocally and specifically stipulating the rights and obligations of those bodies authorized to acquire and use Rural land-holdings in the regional state, have an irreplaceable part in the effort undertaken to be exonerated from poverty, within the ambit of the Rural development and prosperity to be realized in a fair course thereof;

WHEREAS, the action to get the rural land administration system built upon the full participation of the land-holders themselves with a special emphasis as to the peculiar benefits of women, incapables and orphans is believed to further facilitate the pace of the speedy development,

WHEREAS, it has been necessary to put in place a working system with a transparent and responsible land administration and use so as to ensure the maintenance of land fertility and thereby protection of the environment along with the sustainability of the land Administration itself, having enjoyed the overall support of the general public;

WHEREAS, it has been found appropriate to create favorable conditions which might enable land holders to materilize sustainable development and investment promotion in the regional state by integrating their labor, wealth and creative abilities following the

የአማራ ክልል መስተዳድር ም/ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 133/1998 ዓ/ም /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

## ??? ???

## ? ???

### 1. ?? ? ???

ይህ ደንብ " የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓት ማስፈፀሚያ ክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ ቁጥር 51/1999 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ? ???

1. በዚህ ደንብ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉትና "አርሶ አደር"፣ "ባለስልጣን"፣ "ልጅ" "ተጧሪ"፣ "የወል ይዞታ"፣ "የቤተሰብ አባል"፣ "የመንግሥት ይዞታ"፣ "የይዞታ መብት"፣ "የግል ይዞታ"፣ "የጋራ ይዞታ"፣ "የቀበሌ ነዋሪ"፣ "የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ" "የመሬት ተጠቃሚ" "ሰው" "የህዝብ አገልግሎት" "የገጠር መሬት አስተዳደር"፣ "የገጠር መሬት"፣ "ኪራይ" "የመጠቀም መብት" "መሬት ማስለቀቅ" እና "የመሬት ባለይዞታ" የተሰኙት ቃላትና ሀረጎች በተሻሻለው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና

ownership mentality to be produced as the result of the land holding;

NOW, THEREFORE, the council of the Amhara Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of Art.58 sub-art.7 of the revised Regional constitution and Art. 33 sub-art.1 of the revised Rural Land Administration and use Determination Proclamation No. 133/2006, hereby issues this regulation.

## PART ONE

## General

### 1. Short Title

This regulation may be cited as "The Rural Land Administration and Use System Implementation, Council of Regional Government Regulation No. 51/2007."

### 2. Definitions

1. Such terms and phrases used in this regulation as "Farmer", "Authority", "Child", "pensioner", "common Holding", "Family member", "State Holding", "Kebele resident", "Land use plan", "Land user", "Person", "Public service", "Rural Land Administration", "Rural land", "Rent", "use Right", "Expropriation from land holding" and "Land Holder" shall have the definitions given to them under art.2 of the Revised Regional State Rural Land Administration and use determination proclamation No, 133/2006.

አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 133/1998 ዓ/ም አንቀጽ 2 ሥር የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

2. የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ፡-

ሀ/ "ባለሀብት" ማለት የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥቶ ግብርናውን ከኢንዱስትሪው ጋር በማስተሳሰር ዘርፉን ወደ ላቀ ደረጃ የሚያሸጋግር እቅድ በመንደፍ መዋዕለ ንዋዩን በገጠር መሬት ላይ እያፈሰሰ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባለው ስራ ላይ የተሰማራ እና የውጭ ምንዛሬን የሚያስገኝ ማናቸውም ሰው ነው፡፡

ለ/ "የኢንቨስትመንት ይዞታ" ማለት በአንድ ቀበሌ ውስጥ የኢንቨስትመንት ፍቃድ በተሰጠው ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ድርጅት ስም ተመዝግቦ ለተወሰነ ጊዜ የመጠቀም መብት የተጠበቀበት የገጠር መሬት ነው፡፡

ሐ/ "ብሔራዊ አገልግሎት" ማለት ለተወሰነ ጊዜ አካባቢውን ትቶ በመሄድ የሚሰጥ ወታደራዊ አገልግሎት ወይም ድንገተኛ አደጋን ለመቋቋም የሚሰጥ አገልግሎት ወይም በምርጫ ወይም በምደባ ተለይቶ ለታወቀ ጊዜ በመደበኛ ሠራተኛነት በመንግሥት አስተዳደር መሳተፍ ነው፡፡

መ/ "ገማች" ማለት በይዞታ ላይ የለማን ንብረት የካሳ መጠን ለመተመን ልምዱ ወይም እውቀቱ ወይም ሁለቱም ያሉት ሆኖ

2. Unless the context otherwise requires;

A. "Investor" shall mean any person who has obtained an investment license and thereby engages in an activity of economic significance through channeling his financial wealth on to the rural land and helping generate hard currency, having to that effect formulated a plan capable of promoting the sector into a higher level by way of linking the agriculture along with the industry.

B. "Investment Holding" shall mean plot of Rural land registered in the name of an individual, group, or organization licensed as investor in a certain kebele and whose use-right is upheld for a definite period of time.

C. "National service" shall mean any military service rendered for a definite period of time by departing from one's locality or a service rendered to cope with an emergency operation having to do with a certain calamity or participation in a public administration as a regular employee, be it in the form of through an election or assignment for a specified duration.

D. "valuer" shall mean an institution or expert working in a private or public institution who has the knowledge or experience or both

በባለስልጣኑ የሚሰየም በግል ወይም በመንግስት ተቋማት ውስጥ የሚሰራ ባለሙያ ወይም ተቋም ነው።

ሠ/ "ካሳ" ማለት የመሬት ይዞታውን እንዲለቅ የሚወሰንበት ባለይዞታ በመሬቱ ላይ ላሰፈረው ንብረት በዓይነት ወይም በገንዘብ ወይም በሁለቱም የሚፈፀም ክፍያ ነው።

ረ/ "ቀመር" ማለት ይዞታውን እንዲለቅ ለሚወሰንበት ባለይዞታ የሚከፈለውን ካሳ ወጥ በሆነ መንገድ ለመገመት የሚያስችል የአሰራር ቅደም ተከተል ነው።

ሰ/ "አዋጅ" ማለት ተሻሽሎ የወጣው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 133/1998 ዓ.ም ነው።

## 3. ??? ? ?

ደንቡ ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል:-

1. በአዋጁ ውስጥ የተመለከቱት የገጠር መሬት ባለይዞታ መብቶችና ግዴታዎች በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ የመሬት አስተዳደር ስርዓቱ የክልሉን ዘላቂ የግብርና ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እንዲያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤

2. የአፈሩን ለምነትና የአካባቢውን ደህንነት የሚያስጠብቅ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት

to assess the amount of compensation for an asset developed on a land holding, having been designated by the authority.

E. "Compensation" shall mean a payment made payable in kind or cash or both to the land holder who may be dispossessed of his holding in return for an asset established thereon.

F. "Formula" shall mean a set of working procedure enabling one to assess the amount of compensation payable to the holder who might be required to relinquish his holding in a uniform manner.

G. "Proclamation" shall mean the Revised Rural Land Administration and use Determination proclamation No. 133/2006

## 3. Objective

The regulation shall have specific objectives indicated herebelow:

1. To create favorable conditions enabling the land administration system to promote long-lasting agricultural product and productivity of the regional state by causing the full implementation of the rights and obligations pertaining to the rural land holders as are stipulated under the proclamation;
2. To put in place a land use system instrumental for the preservation of the soil fertility as well as

ማስፈን፣

3. እያንዳንዱን የመሬት ባለይዞታና የይዞታውን አጠቃላይ ባህርይ ያካተተ የመረጃ ስልት በመንደፍ በክልሉ ውስጥ ፍትሀዊ የመሬት አስተዳደር ስርዓትን ዕውን ማድረግ፣

4. ለሴቶች፣ ለአቅመ ደካሞችና ለወላጅ አልባ ህፃናት የተደረገላቸውን ልዩ ጥበቃ በማረጋገጥ ለመልካም አስተዳደር ስርዓት መስፈን ጉልህ አስተዋጽኦ ማበርከት እና

5. ለኢንቨስትመንት የሚውለውን የገጠር መሬት አቅርቦት ማሻሻልና ውጤታማነቱን መከታተል።

## ??? ???

## ? ?? ?? ???? ?? ???

## ? ??? ?????

### 4. ? ?? ?? ??? ? ??

1. በሀገሪቱ ህግ መሠረት ለአካለ መጠን የደረሰ ማንኛውም ሰው በግብርና ሥራ የሚተዳደር ወይም ለመተዳደር የሚፈልግ የገጠር ነዋሪ መሆኑ የታወቀ እንደሆነ በክልሉ ውስጥ የመሬት ይዞታ በነፃ የማግኘት መብት አለው።

2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ዓላማ ለትምህርት፣ ለብሔራዊ አገልግሎት ወይም ለሌላ ለማናቸውም ተመሣሣይ ተግባር በጊዜያዊ ተልዕኮ ምክንያት በከተማ የሚገኝ ሰው ወይም የከተማ ኑሮውን ትቶና ወደገጠር

environment safety;

3. To realize an equitable land administration system in the regional state by devising a mechanism of documentation incorporating each and every land holder and the overall nature of the holding so occupied;

4. To render a significant contribution for the prevalence of good governance by materializing the special protection accorded to women, incapables and orphans and;

5. To improve performance as regards the provision of rural land that may be utilized for investment purposes and thereby follow up its effectiveness.

## PART TWO

## IMPLIMENTATION OF THE RIGHTS OF LAND ACQUISTION AND USE

### 4. The Right to Acquire Land

1. Any person who has attained civil majority in accordance with the laws of the country shall, where it is known that he is a rural resident engaging or wishing to engage in an agricultural activity have a right to freely acquire a land holding in the regional state.

2. For the purpose the provision of sub. Art.1of this article hereof, a person residing in an urban center for education, national service or any other similar duty as a result of a temporary mission or one who may have left his urban life

ተዛውሮ በግብርና ሥራ ለመተዳደር የሚፈልግ ሰው እንደገጠር ነዋሪ ይቆጠራል።

3. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የብዙሃን ማህበራት፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሃይማኖት ተቋማት ተግባራቸው ለትርፍ የሚፈፀም እስካልሆነ ድረስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን የአርሶ አደሮች መሬት የማግኘት መብት በማይፃረር ሁኔታ ለስራቸው የሚጠቀሙበት የገጠር መሬት በይዞታ ሊያገኙ ይችላሉ። ሆኖም ይህንኑ የገጠር መሬት ይዞታ በውርስም ሆነ በስጦታ ለሶስተኛ ወገኖች ሊያስተላልፉ አይችሉም።
4. በግብርና ሥራ ለመሠማራት የሚፈልጉ የግል ባለሀብቶች የሚጠቀሙበት መሬት ከመንግሥት በሊዝ ወይም ከግል ባለይዞታዎች ጋር በሚደረግ ስምምነት በኪራይ የማግኘት መብት አላቸው። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

## 5. ??? ?? ?????

1. በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች መሠረት በግብርና ሥራ እንደሚተዳደር ወይም ለመተዳደር እንደሚፈለግ ገልፆ የሚያመለክት ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው የቀበሌ አስተዳደር ጠይቆ የሚያገኘውና ለተጠቀሰው አገልግሎት የሚያውለው የገጠር መሬት ይዞታ መጠን በዝናብ የሚለማ ማሣን ያካተተ ከሆነ ከ0.25 ና በመስኖ የሚለማ ማሣን ያካተተ ከሆነ ደግሞ ከ 0.11 ሄክታር ሊያንስ አይችልም።

and transferred in to a rural area with an intention to engage himself in an agricultural occupation, shall be considered as a rural dweller.

3. Mass organizations, governmental and non-governmental organizations and religious institutions found in the regional state may, where their duties are not performed for gain**,** acquire rural land holding which they may use for their undertakings, on condition that such a move may not contravene the right of farmers to acquire land as provided under sub-art-1 of this article hereof; provided, however, that they may not transfer same to third parties, either in bequeath or donation.
4. Private investors who desire to engage in an agricultural business shall have the right to obtain land that they may so use, from the government through lease or, from private holders through rental**,** on the basis of an agreement to be concluded with the latter. Particulars shall be determined by a directive.

## 5. How to exercise

1. the size of the rural landholding that any person may acquire by a applying for the same to the pertinent kebele administration having stated that he engages himself or wishes to so engage in an agricultural activity and use it for the aforementioned purpose, in accordance with the provisions of Art.7 sub-art 1 of the proclamation and Art.4 sub-art 1of this regulation, may not be less than 0.25 hectares, where it refers to a plot

of land cultivated by rain and 0.11 hectares, where it refers to the plot of land cultivated by irrigation .

2. መሬት ለማግኘት የሚቀርብ ማናቸውም ጥያቄ ለሚመለከተው አካል የሚቀርበው ይህንን ደንብ ለማስፈፀም ባለስልጣኑ ከሚያወጣው መመሪያ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ቅጽ መሠረት በጽሁፍ ይሆናል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ግለሰብ ለራሱም ሆነ ከቤተሰቡ ጋር በይዞታ የሚሰጠውና ሊኖረው የሚገባው ከፍተኛ የመሬት መጠን በደጋ እና በወይና ደጋ ከ7 ሄክታር እና በቆላ አካባቢዎች ደግሞ ከ10 ሄክታር የበለጠ ሊሆን አይችልም።

4. በትርፍ ላይ ያልተመሰረተ የህዝብ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋሙ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ተቋማትና ድርጅቶች ለተቋቋሙበት ተልዕኮ መሣካት የሚያስፈልጋቸው የገጠር መሬት ይዞታ መጠን ከተሰጣቸው ሥራ ስፋትና ውስብስብነት ጋር በተገናዘበ አኳሃን ተጠንቶ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

5. በዚህ አንቀጽ ከዚህ በላይ የሰፈሩት ድንጋጌዎች ትርፍ መሬት ባልተገኘበት የክልሉ አካባቢ ከቀደምት ባለይዞታዎች ጋር በሚደረግ ድርድር መሬት ከግለሰብ አርሶ አደሮች በኪራይ ውል መሠረት ማግኘትን የሚከለክሉ አይሆኑም።

6. በዚህ አንቀጽ መሠረት መሬትን በይዞታ

2. Any request put forward with the view to acquiring land shall be submitted in writing to the concerned body using the from annexed to the directive to be issued by the authority for the execution of this regulation.

3. Notwithstanding the provision of sub. Art.1 of this article hereof, the maximum size of land that any one may be granted in holding and enjoyed at house-hold or family levels may not exceed seven hectares in the high land and semi-high land and ten hectares in the low land areas respectively.

4. the size of the rural land holding that may be necessary for the legal intuitions and organizations established with the view to rendering non-profit public service, in order to fulfill the mission of their establishment shall be determined by a directive to be issued by the authority, having been studied with a reference to the extent and complexity of the tasks entrusted upon them.

5. The provisions stipulated herein above under this article may not, where no surplus land is available, bar an acquisition of land from individual peasant farmers in rent by negotiating with the former land holders in the Regional state.

6. The right of acquisition of land holding may,

የማግኘት መብት ተግባራዊ የሚሆነው ከዚህ በታች ከተመለከቱት ሁኔታዎች አንዱ ወይም ሌላው ተሟልቶ ሲገኝ ይሆናል:-

ሀ/ ዝርዝሩ በመመሪያ የሚደነገግ ሆኖ የመሬት ሽግሽግ እንዲካሄድ በህዝብ ሲወሰን፣

ለ/ አስቀድሞ በይዞታ ያልተደለደለና በተለያዩ ምክንያቶች ትርፍ ሆኖ የተመዘገበ መሬት መኖሩ ሲረጋገጥ፣

ሐ/ የወል የነበረ የገጠር መሬት ይዞታ ለግል ተጠቃሚዎች እየተሸነሸነ እንዲሰጥና ጥቅም ላይ እንዲውል በህዝብ ሲወሰን።

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ስር የተመለከቱት ሁኔታዎች ካለመኖራቸው የተነሳ መሬት የማግኘት መብትን በተጨባጭ ተግባራዊ ማድረግ ያልተቻለና በክልሉ ውስጥ በየትኛውም አካባቢ ሰፈራ ለማካሄድ የሚያመች በቂ ቦታ መኖሩ የተረጋገጠ እንደሆነ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተን የሠፈራ ፕሮግራም በመንደፍና በማስፈፀም መሬት በይዞታ የሚሰጥበት አማራጭ ሊታይ ይችላል።

## 6. ?? ?? ???? ???? ?? ? ? ??? ?? ??? ??? ??? ??

1. የአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠቀበ ሆኖ በክልሉ ውስጥ የመሬት ሽግሽግ በልዩ ሁኔታ ሊካሄድ የሚችለው በዚህ ደንብ ከተወሰነው አነስተኛ የይዞታ መጠን በላይ የሆነ መሬት ያላቸውና ቢያንስ

pursuant to this Article, be applicable where one or the other of the conditions indicated herein below shall be satisfied:

A. with the details to be stipulated in a directive, where it is publicly determined that land re-distribution is to take place:

B. Where it is ascertained that there exists an extra plot of land which is not already allocated in holding and registered as a surplus land, due to a variety of reasons;

C. Where it is decided by the public at large that a communal rural land holding is to be distributed for and utilized by individual users.

7. Where it has been objectively impossible to materialize the right of acquision of land holding due to an absence of the conditions specified under sub, Art. 6 of this article hereof, and where it is ascertained that there exists sufficient land readily available for possible re-settlement in the regional State, An alternative of land provision may be considered by formulating and executing a voluntary re-settlement scheme thereof.

## 6. Re-distribution to be established on the consent of the land holders

1. Without prejudice to the provision of Art. 8 sub, art 1 of the proclamation, land Re-distribution may be carried out in the regional stat under exceptional circumstance, where those who possess land in excess of the size of

ሰማንያ ከመቶ የሚሆኑት የአንድ ቀበሌ ነዋሪዎች በጉዳዩ ላይ ተስማምተው ጥያቄያቸውን ለባለስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት በፅሁፍ ሲያቀረቡ ይሆናል።

2. ሽግሽጉን የሚያፀድቀው ስምምነት ተፈፃሚ የሚሆነው ውሣኔውን ደግፈው ድምፅ በሰጡት የመሬት ባለይዞታዎች ላይ ብቻ ነው። ስለሆነም ማንኛውም የመሬት ባለይዞታ መሬት ይሸጋሸግ በሚለው ጉዳይ በተጠራው ስብሰባ የተገኘና በውይይቱ የተሳተፈ ቢሆንም ውሣኔውን በመደገፍ ድምጽ እስካልሰጠ ወይም ይህንኑ እስከተቃወመ ድረስ የታቀደው ሽግሽግ በራሱ የይዞታ መሬት ላይ ተፈፃሚ አይሆንበትም።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች መሠረት የመሬት ሽግሽግ ይካሄድ ወይም አይካሄድ የሚል ውይይት በሚደረግበት ስብሰባ ላይ መሬት የሌላቸውና ከአነስተኛ የይዞታ መጠን በታች የሆነ የመሬት ይዞታ ያላቸው የቀበሌው ነዋሪዎች በስብሰባው ላይ ሊገኙ አይችሉም፣

4. የመሬት ሽግሽግ ይደረግ የሚለው ውሣኔ ተፈፃሚ የሚሆነው ባለስልጣኑ ይህንን ደንብ ተከትሎ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሲሆን ሽግሽጉ የመሬት መበጣጠስን የሚያስከትል ሆኖ ካገኘው ውሣኔውን ላይቀበለው ይችላል።

5. የህዝብን ውሣኔ ለማስፈፀም ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መሬት እንዲከፋፈል የተደረገ እንደሆነ መሬቱ

the minimum prescribed by this regulation and at least 80% of the kebele inhabitants have consented on the subject and submitted in writhing their request for same to the authority's Woreda representative office.

2. The Agreement approving the Re- distribution shall be applicable on those land holders who may have voted in support of the decision; provided, however, that such a planned Re-distribution may not affect any land holder who has shown up and participated in a gathering called upon to deliberate on land re-distribution so long as he; has voted for the motion in support of the decision or rejected same.

3. Landless kebele residents and those who possess holdings below the prescribed minimum may, not Pursuant to the provisions of sub, Art.1 and 2 of this Article hereof, be able to attend the gathering to deliberate on the issue as to whether land Re-distribution is to take place or not..

4. The decision for land Re-distribution shall be applicable on the basis of a directive to be issued by the Authority subsequent to this regulation; provided, however, that the authority may not accept such decision should it finds to the redistribution likely cause land fragmentation**.**

5. Where land has duly been Re- distributed in accordance with the directive to be issued by the authority with the view to executing public

ተቀንሶ የሚወሰድበት ባለይዞታ የመሬት መበጣጠስን የሚያስከትል ካልሆነ በስተቀር የፈለገውን ክፋይ መርጦ የማስቀረትና በመሬቱ ላይ ላፈራው ሀብት መሬቱን ከሚረከበው ሰው ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው።

6. በዘመናዊ መስኖ ከሚለማ መሬት ላይ ለመስኖ መሠረተ ልማት አውታሮች ግንባታና ለሌሎች መሰል አገልግሎቶች ሲባል ይዞታቸውን ያጡትን ባለይዞታዎች ጥቅም በሚያስከብር መልኩ ሽግሽጉ ሊካሔድ ይችላል፣

7. ማንኛውም ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ በዘመናዊ መንገድ የሚለማ የመስኖ መሬትን በሚመለከት ሽግሽግ እንዳይካሄድ መከልከል አይችልም፣

8. መሬታቸው በዘመናዊ የመስኖ መሠረተ ልማት አውታሮች ግንባታ ምክንያት የተወሰደባቸው ባለይዞታዎች በመስኖ ከሚለማው መሬት ውስጥ በሽግሽግ እንዲያገኙ ይደረጋል። ይህንኑ እስከሚያገኙ ድረስም ከመሬታቸው ያገኙት ከነበረው የምርት መጠን ጋር የሚመዛዘን ካሣ በቅድሚያ ከመንግሥት የማግኘት መብት ይጠበቅላቸዋል።ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

9. የመስኖ መሬት ሽግሽግ አግባብ ባለው ወረዳ አስተዳደር የቅርብ ክትትል በባለስልጣኑ ተጠሪ ጽ/ቤት እየታገዘ የመስኖ ልማት

decisions, a land holder, whose land holding, has been reduced and taken there from shall, of such action is not to cause fragmentation, have the rights to retain the portion of his own choice as well as obtain from the person taking over the land prior compensation commensurate to the value of the assets produced thereon.

6. the Re- distribution may be undertaken with respect the land to be developed using modern irrigation in a manner that satisfies The interests of those holders having lost their holdings for the construction of irrigation, Infrastructure and other similar services.

7. Any holder or user may not prohibit redistribution form having been carried out as regards land to be developed with modern irrigation.

8. Those holders whose land is taken away due to the construction of modern irrigation infrastructure shall be provided with their share by way of Re-distribution out of the land to be developed through irrigation. To that effect, their right to obtain from the government prior compensation commensurate to the amount of the product which happened to be gained from their land shall be respected until such time that they are provided with same. Particulars shall be determined by a directive.

9. An irrigated land redistribution shall be carried out through the instrumentality of the pertinent committee members to be elected by the

ተጠቃሚዎች በሚመርጧቸው የኮሚቴ አባላት አማካኝነት ይካሄዳል፣

beneficiaries of the irrigation development with the assistance of the Authority's woreda representative office along with the closest follow up of the woreda administration concerned.

10. የመስኖ መሬት ሽግሽግ በሚካሄድበት ጊዜ የመሬት መበጣጠስን የሚያስከትል ሆኖ እስካልተገኘ ድረስ ባለ ይዞታው የመረጠውን ክፍል እንዲወስድ ይደረጋል።

10. Where an irrigated land redistribution is underway the land holder shall have the opportunity to take the plot of his choice in so for as such an action does not potentially cause land fragmentation thereof.

11. የመስኖ መሬት ሽግሽግ ሲካሄድ በተቻለ መጠን የአርሶ አደሩን ይዞታ የማቀራረብ ተግባር ይከናወናል።

11. Where redistribution takes place with regard to an irrigated land, there shall be carried out an activity of consolidating, individual peasants, land holdings, as much as possible.

12. የመስኖ መሬት ሽግሽግ በሚካሔድበት ጊዜ ቋሚ ሰብል ያለበት መሬት የደረሰው ማንኛውም አርሶ አደር ለቀድሞው ባለይዞታ ተገቢውን ካሣ በቅድሚያ መክፈል ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ይኸው ግዴታ ያለበት ባለይዞታ ካሣውን በአንድ ጊዜና በቅድሚያ የመክፈል አቅም እንደሌለው ገልፆ በጽሁፍ ሲያመለክትና ይኸም በባለሰስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት ሲታመንበት የቅድሚያ ካሣ ክፍያውን መንግሥት እንዲፈፅም ተደርጐ የከፈለውን መጠን ከባለግዴታው የመሰብሰብ መብት ይኖረዋል።ዝርዝሩ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

12. Without prejudice to the fact that any farmer who received land covered with the perennial crops is duty-bound to pay in advance proper compensation to the previous holder, where the said holder applies in writing that he cannot afford to pay at once the compensation beforehand such an application is accepted by the Authority's Woreda representative office, the government shall, after having made the payment of compensation, in advance have the right to collect the amount of expenditure from the debtor. Particulars shall be determined by a directive to be issued for the implementation of this regulation.

13. የመስኖው ተጠቃሚዎች ሙሉ ስምምነታቸውን ካልሰጡ በስተቀር የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ይህ ደንብ ከመፅናቱ በፊት በተገነቡ የዘመናዊ መስኖ ግንባታ መሬቶች

13. The provisions of this article hereof shall not be applicable to the modern irrigation construction lands which are known to have been constructed prior to the coming into force

ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

## 7. ???? ?? ? ? ? ? ????? ??? ??

በክልሉ ውስጥ ለአንድ ሰው የሚሰጠው ዝቅተኛ የማሣ መጠን በዝናብ ለሚለማ መሬት ከ0.2 እና በመስኖ የሚለማ መሬትን የሚመለከት ከሆነ ደግሞ ከ0.6 ሄክታር በታች ሊሆን አይችልም።

## 8. ?? ?? ? ?? ? ??? ????

የገጠር መሬት በይዞታ የተሰጠው ማንኛውም ሰው አፈፃፀሙ የመሬት መበጣጠስን የሚያስከትል ሆኖ እስካልተገኘ ድረስ ይዞታውን ከሌላ ሰው ጋር የመለዋወጥ መብት አለው። ሆኖም ይህ ልውውጥ የሚፀናው አግባብ ላለው የባለስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት ቀርቦ ሲመዘገብ ብቻ ይሆናል።

## 9. ??? ?? ?????

1. በአዋጁ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 5 ሥር በተደነገገው መሠረት ስለ መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ከሚያወጣው አካል መሬቱን የሚጠቀምበት አግባብ በውል ተለይቶ በፅሁፍ ካልተገለፀለት በስተቀር ማንኛውም ባለይዞታ ይዞታውን የሚመለከት የአጠቃቀም ዕቅድ እስኪዘጋጅ ድረስ መሬቱን ለቤት መስሪያ፣ ለእርሻ፣ ለእንስሳት እርባታ፣ ለደን ልማት ወይም ከእነዚሁ ጋር ተዛማጅነት

of this regulation unless the beneficiaries of the said irrigation have given their full consent.

## 7. Determination of the Minimum Plot of Land

The minimum size of a plot of land to be granted for any person in the Regional State may not be less than 0.2 if it is cultivatable by rain and 0.06 hectares if it is cultivatable through irrigation respectively.

## 8. Exchange of Land Holdings

Any person who is granted rural land in holding shall have the right to exchange his possession with that of another holder so long as the implementation of such an exchange does not result in a possible land fragmentation; Provided, however, that the said exchange is to be effective only upon its submittal to and registration by the pertinent Authority’s woreda representative office.

## 9. Utilization of Land

1. Unless he has been provided with a clear identification and sufficient prescription in writing with regard to the use of his land form the body competent to formulate land use plans as per the provisions of art. 13 of sub- Art.5 of the proclamation, any land holder may be able to utilize his plot of land for house construction, farming, animal husbandry, forestry, or other related activities thereto until such time that land

ላላቸው ሌሎች ተግባራት ሊያውለው ይችላል።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ መሬቱን በህግ ለተከለከሉ አደንዛዥ ዕፅዋት ማልሚያነት መገልገል አይፈቀድም። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

use plan shall have been prepared as regards his holding.

2. Without prejudice to the provision of sub.Art.1 of this Article hereof, it shall not be permitted to use such land for the cultivation of narcotic plants which are forbidden by law. Particulars shall be determined by a directive.

## 10. ? ??? ?? ?? ? ??? ? ??

1. በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ያገኘ ማንኛውም ባለይዞታ በተለያዩ ስፍራዎች ያሉትን ማሣዎቹን ለማቀራረብ ወይም ኩታ ገጠም ለማድረግ ይቻለው ዘንድ ከሌላ የመሬት ባለይዞታ ጋር በፈቃደኝነት ሊለዋወጥ ይችላል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገውን መብት ተፈፃሚ ለማድረግ የመሬት ባለይዞታዎች የህግ ምክርና የቴክኒክ ድጋፍ እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ አግባብ ያለው የባለስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት አስፈላጊውን ድጋፍ በነፃ ይሰጣል። ዝርዝሩ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

3. የመሬት ባለይዞታዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት መሬትን ኩታገጠም ለማድረግ የመሬት ልውውጥ ሲያካሂዱ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በነፃ ይታደስላቸዋል።

## 10. Consolidation of Land Holdings

**1.** Any holder, having acquired the right to use rural land may voluntarily exchange his plots of land situated in various localities with another land holder in order to consolidate same or find them contiguous with one another.

**2.** The Authority pertinent woreda representative office shall freely render the necessary support in order to implement the right stipulated under sub-Art. 1 of this article hereof, where the land holders approach and ask for legal advise and technical assistance. Particulars shall be determined by a directive to be issued by the authority.

**3.** Where land holders undertake an exchange of land holding with the view to consolidating pursuant to sub. Art 1 of this Article hereof, they shall obtain renewal of their land holding certificate free of charge.

# ??? ???
# መሬት ነክ መብቶች ስለሚተላለፉባቸው መንገዶች

## 11. ?? ?? ??? ? ??? ?? ?? ??? ?????

1. በዚህ ደንብ መሠረት የገጠር መሬት ባለይዞታ የሆነ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ይህንኑ የይዞታ መብቱን በግብርና ሥራ ለሚተዳደር ወይም መተዳደር ለሚፈልግ የኑዛዜ ተጠቃሚ ሊያስተላለፍ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም ተናዛዡ በሞተበት ወቅት የራሱ የሆነ ቤተሰብ ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ያሉትና አድራጎቱ ቤተሰቡን ወይም ልጆቹን ከህጋዊ ወራሽነት የሚነቅል ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ኑዛዜው በህግ ፊት ተቀባይነት አይኖረውም።
3. የመሬት ይዞታ መብቱን በኑዛዜ አስተላልፎ የሞተ ሰው ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ባይኖሩትም ኑዛዜውን በሰጠበት ወቅት የትዳር ጓደኛ የነበረውና የመሬት ይዞታና የመጠቀም መብቶቹን በኑዛዜ ያስተላለፈው ለዚሁ ለትዳር ጓደኛው ሣይሆን ለሌላ ሰው የሆነ እንደሆነ ከሞተበት ቀን ጀምሮ ለሚቀጥሉት ሁለት የምርት ዓመታት ይዞታው በህይወት ባለው የትደር ጓደኛ እጅ ሆኖ የመጠቀም መብቱን በተመለከተ ኑዛዜው ከመፈፀም ታግዶ ይቆያል። ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ ግን በኑዛዜው መሠረት የመጠቀም

# PART THREE
# WAYS OF TRASFERRING LAND RELATED RIGHTS

## 11. Transfer of Land Holding rights in Bequeath

1. Any natural person who happens to be a rural land holder in accordance with this regulation may transfer his holding rights to a beneficiary by will who engages or wishes to engage in agricultural works.
2. Notwithstanding the provision of sub. Art.1 of this Article hereof, where a will making person already has his own family or minor children at the time of his death and his deed is likely to isolate his family or his children from legal inheritance, his will shall not be valid at law.
3. Where a person, having died after transferring his holding right by will does not have minor children but rather a spouse while declaring the will and where he has transferred his land holding and use rights by will to persons another than his spouse, the land holding shall remain in the hands of his surviving spouse for two consecutive harvesting years as of the date of his death and as for as the use right is concerned, the will shall stay suspended short of execution provided, however that after the aforementioned period of time such use right shall be conveyed to the designated beneficiary in a distinctly identifiable manner,

መብቱ ተለይቶ ለኑዛዜ ባለመብቱ የሚተላለፍ ይሆናል።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር የሰፈረው ድንጋጌ ቢኖርም በህይወት የቀረው የትዳር ጓደኛ መሬቱን መጠቀም የሚችልበት የሁለት ዓመት ጊዜ ገደብ ከመሙላቱ በፊት በተራው የሞተ እንደሆነ የመጀመሪያው ሟች ቀድሞ የተናዘዘለት ሰው የመጠቀም መብቱን ወዲያውኑ ሊሰራበት ይችላል።

5. ሟች የተናዘዘው በመሬት የመቀጠም መብቱን በተመለከተ ሣይሆን በመሬቱ ላይ ያፈራውን ሀብት ብቻ ለማስተላለፍ የሆነ እንደሆነ ከዚህ በላይ የተመለከተው ገደብ ተፈፃሚ አይሆንም። ዝርዝር አፈፃፀሙ በመመሪያ ይወሰናል።

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም ሟች የይዞታ መብቱንና ለተወሰነ ጊዜ የመጠቀም መብቱን ለተለያዩ ሰዎች በኑዛዜ ሊያስተላልፍ ይችላል። ሆኖም የመጠቀም መብቱ ፀንቶ እንዲቆይ የተወሰነለት ጊዜ ሲያበቃ የኑዛዜ ባለመብቱ ከመጠቀም መብቱ ባለፈ የመሬት ባለይዞታነቱን ያገኛል።

7. ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ ሣይናዘዝ የሞተ እንደሆነ ወይም ኑዛዜው በህግ ፊት የማይፀና ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የመሬት ይዞታው እንደቅደም ተከተላቸው ከዚህ በታች ለተመለከቱት የቅርብ ዘመዶቹ ይተላለፋል:-

4. Notwithstanding the provision of sub.art.3 of this article hereof, where the surviving spouse himself dies prior to expiry of the two years period for the possible use of the land, the person, to whom a will is made by the former deceased person may exercise his use right forthwith.

5. Where the deceased exercise person makes a will to transfer solely the asset produced on the land, distinct from the use right, the time herein above shall not be applicable. The detailed implementation shall be determined by a directive.

6. Notwithstanding the provision of sub. Art. 1 of this Article hereof, a deceased person may transfer by will his holding right or his use right for a limited period of time to several persons. Provided, however, that the beneficiary at will shall gradually acquire the status of a land holder once the defined period of time for the exercise of the use right has expired.

7. Where any rural land holder dies prior to making a will or the will so declared is found to be invalid at law, the land holding belonging to him shall be transferred to his close relatives, having regard to the order of as indicated here in below.

ሀ/ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆቹ፣ ልጅ ከሌለው የቤተሰብ አባላቱ፣

ለ/ ምንም አይነት መሬት የሌላቸው ሆነው ለአካለ መጠን የደረሱ ልጆች ወይም ሌሎች የቤተሰብ አባላት በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ ወይም ለመተዳደር የመረጡ መሆናቸው እስከተረጋገጠ ድረስ፤

ሐ/ የራሣቸው መሬት ቢኖራቸውም በግብርና ሥራ የሚተዳደሩና ለአካለ መጠን የደረሱ ልጆች፤

መ/ ለአካለ መጠን ያልደረሱም ይሁኑ የደረሱ ልጆች ወይም የቤተሰብ አባላት ወይም አብሮ ነዋሪ ተንከባካቢዎች የሌሉ እንደሆነ በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ ወይም ለመተዳደር የሚፈልጉ ወላጆች።

8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 ፊደል ተራ ቁጥር መ ሥር የተደነገገው ቢኖርም ባለይዞታው ሲሞት ባለትዳር የነበረ ከሆነ ከሞተበት ቀን ጀምሮ በህይወት የቀረው የትዳር ጓደኛ መሬቱ በሚገኝበት ቀበሌ ክልል መኖሩን ከቀጠለ አዲስ ጋብቻ እስኪፈፅም፣ ካላገባ ደግሞ በሞት እስኪለይ ድረስ ሲጠቀምበት ይቆያል። ሆኖም በዚያው ቀበሌ ውስጥ መኖሩን ሲተው፣ አዲስ ጋብቻ ሲፈፅም ወይም በሞት ሲለይ በመሬት የመጠቀም መብቱ የሟች ህጋዊ ወራሾች ለሆኑት ወላጆች ይተላለፋል።

9. ወራሾች በቁጥር ከአንድ በላይ በሚሆኑበት

A. His minor children, or in the absence of same, his family members;

B. His sons and daughters of full age or other family members having virtually no land and yet engaging or preferring to engage in an agricultural work as the means of their lively hood;

C. Those sons and daughters of full age, although, they already have their own land holdings, where such persons so engage in an agricultural work;

D. parents who engage or wish to engage in an agricultural work, where there are no minor children, grownups, family members or caretaker individuals living together with the deceased.

8. Notwithstanding the provision of sub. Art 7 (D) of this Article hereof, where the land holder has left a spouse at the time of his death, the surviving spouse shall continue using the land as of the date of the farmer's death if he (she) continues to reside in the same kebele or until he /she/ concludes new marriage if that is not to be the case, until he (she) passes away; provided, however, if he (she) quits residing that kebele, concludes marriage or dies, such use right with respect to the land shall be transferred to parents who are the legal heirs of the deceased.

9. They may not have the right to share such

ጊዜ በውርስ ያገኙትን የገጠር መሬት በመከፋፈል ወይም የጋራ ይዞታቸው በማድረግ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ሆኖም ይዞታው ሲከፋፈል እያንዳንዱ ክፋይ በዝናብ ለሚለማ መሬት ከ0.2 ሄክታርና በመስኖ ለሚለማ መሬት ደግሞ ከ0.06 ሄክታር በታች የሆነ እንደሆነ ወራሾች ይዞታውን በጋራ መጠቀም እንጅ በነፍስ ወከፍ የመከፋፈል መብት አይኖራቸውም።

holding in an individual manner instead of collective utilization, if each plot of land is, in case division, to be less than 0.2 hectare cultivable by rain and 0.06 hectares cultivatable by irrigation respectively.

10. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 9 ሥር የሰፈረው ድንጋጌ በባልና ሚስት ፍቺ ጊዜ በሚካሄደው የመሬት ክፍፍል ላይም በተመሣሣይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

10. The provision stipulated under sub Art 9 herein above shall mutatis mutandis apply to the division of land holdings which might be undertaken at the time of divorce.

11. የመሬት ይዞታው ስፋት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 ሥር ከተደነገገው በታች ከመሆኑ የተነሣ ሊከፋፈል የማይችልና ፍች የፈፀሙት ተጋቢዎች በጋራ ለመጠቀም ያልተስማሙ እንደሆነ መሬቱን ለኪራይ የመስጠት፣ ከሌላ ሰው ጋር የመለዋወጥ፣ አንደኛው ወገን በተናጠል እንዲጠቀምበት የማድረግ ወይም ለሶስተኛ ወገን የማስተላለፍ አማራጭ ይኖራቸዋል።

11. Where the size of land is not virtually divisible due to its being less than that provided under sub. Art 9 of this Art. hereof and the divorced spouses have failed to agree as to its collective utilization they shall have alternatives to offer it for rent, exchange same with that of an other person, cause it to be used by either of them or transfer it to a third party.

12. የገጠር መሬትን በውርስ የማግኘት መብት የተጠበቀለት ማንኛውም ሰው የመሬት ይዞታውን ሲወርስ የሚኖረው ጠቅላላ የመሬት መጠን በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር ከተወሰነው የመሬት ይዞታ ጣሪያ በላይ ሊሆን አይችልም።

12. The total size of the land to be possessed by any person, for whom the right to acquire rural land holding in bequeath has been guaranteed, may not, at the time of inheritance, exceed the ceiling prescribed under Art 5 sub-Art.3 of this regulation hereof.

13. የሟችን የመሬት ይዞታ በኑዛዜ ወይም ያለኑዛዜ የሚወርሱ ሰዎች ያልተገኙ እንደሆነ መሬቱ በሚመለከተው ቀበሌ

13. In the absence of those persons eligible to inherit the land holding of the deceased either by will or other wise, such land shall

የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ አማካኝነት በትርፍነት ተመዝግቦ ለአዲስ መሬት ጠያቂዎች ይከፋፈላል።

14. ሟች በሞተበት ወቅት ህጋዊ የመሬት ይዞታው በኪራይ ውል ተሰጥቶ ከሆነ በውላቸው መሠረት ተከራዮችን ከመጠቀም አያግዳቸውም።

## 12. ?? ?? ?? ??? ? ?? ???? ??? ???? ? ??

1. ማንኛውም የመሬት ባለይዞታ በያዘው መሬት ላይ ያለውን የመጠቀም መብት በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ለማንኛውም ሰው በኪራይ ውል ሊያስተላልፍ ይችላል።
2. ከሶስት ዓመት ለበለጠ ጊዜ የሚደረግ የመሬት ኪራይ ውል በፅሁፍ መደረግና መሬቱ ለሚገኝበት የባለስልጣኑ ወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት ቀርቦ መመዝገብ ይኖርበታል። ከተጠቀሰው ጊዜ በላይ የሚቆይና በቃል የተደረገ የኪራይ ውል በዚህ ደንብ መሠረት የማይፀናና ተቀባይነት የሌለው ነው።
3. በፅሁፍ የተደረገ ማናቸውም የመሬት ኪራይ ውል ሰነድ እንደ ነገሩ ሁኔታ በዘመናዊም ሆነ በአካባቢው ባህላዊ መሣሪያዎች ተለክቶ የሚደረስበትን የመሬቱን ስፋት፣ ውሉ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፣ የኪራዩን መጠንና

be registered as constituting surplus resource and hence distributed to the use of new land seekers through the agency of the relevant kebeke land administration and use committee.

14. Where a deceased's lawful land holding is rendered by rent under a contract at the time of his death such an action may not prevent the contractors from using the land in line with their contractual agreements.

## 12. Conditions of Providing Land use Right through Rent

1. Any land holder may, pursuant to the proclamation and this regulation, transfer to any one his use right he has established on the land on the basis of rental contract.
2. Any land rental contract which may be entered in excess of three years shall be made in writing and registered after where such land is situated having been submitted to the Authority's woreda representative office. Provided, however, that such contract may not be valid and effective, if it has been made orally and for the period longer than the one stipulated hereinabove**.**
3. Any contractual document relating the land rent made in the writing shall, having regard to the circumstances area of the land reachable having been measured by modern or local instruments, of customary nature the

ክፍያው የሚፈፀምበትን አግባብ መግለፅ አለበት።

4. የትኛውም የመሬት ኪራይ ክፍያ ከመሬቱ በሚገኝ ሰብል፣ በየምርት ወቅቱ ባለይዞታው በሚሰጥ አበል ወይም በአንድ ጊዜ ወይም በየዓመቱ ተቆርጦ በሚሰጥ የእህል ወይም የገንዘብ ክፍያ ወይም በሌላ ተመሣሣይ ጥቅም ላይ ተወስኖ የሚፈፀም ሊሆን ይችላል።
5. የግል ባለሀብቶች መሬት ከመንግሥት የሚከራዩበት ከፍተኛ ዘመን በመመሪያ ይወሰናል። ሆኖም በአዋጁ መሠረት በጠቅላላው ከ25 ዓመት የበለጠ ሊሆን አይችልም።
6. በዚህ ደንብ መሠረት ለአሥር ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ተገብቶ የነበረን የኪራይ ውል ተከራዩ ለማደስ የሚፈልግ ከሆነ የኪራይ ዘመኑ ሊያበቃ አንድ ዓመት ሲቀረው ውሉን ለማደስ እንደሚፈልግ ጠቅሶ ለባለይዞታው በፅሁፍ ማሣወቅ አለበት። አከራዩም ጥያቄው በደረሰው በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የበኩሉን ማስታወቂያ ካልሰጠ ውሉን ቀድሞ በነበረበት ሁኔታ ለማደስ እንደተስማማ ይቆጠራል።
7. ማናቸውም የመሬት ይዞታ ለተለያዩ ሰዎች በኪራይ ውል የተሰጠ እንደሆነ ውሉን በመጀመሪያ ቀርቦ ያስመዘገበው ወገን

duration of the contract validity and amount of the rent as well as modality of the payment thereof.

4. Any payment of land rent may, having been determined on crop produced from the land, allowance given to the holder every harvesting season, or payment in grain or in cash given at once or divided annually or on any other similar benefit, be disbursed.
5. The maximum period of time that private investors may rent land from the government shall be determined by a directive. Provided, however, that pursuant to the proclamation, it may not be more than 25 years in general term of agreement.
6. Pursuant to this regulation hereof, where the lessor wants to renew the rent agreement entered into for ten (10) or more than ten (10) years, he shall, having stated that he wants to renew the contract ahead of 1 year before the termination of term of renting period of time, notify in writing to the holder. Unless the lessee forwarded his own notification to the lessor within 6 months since he has received the request, it shall be regarded as he has agreed to renew the agreement as the condition of contract they had earlier.
7. Where any land holding has been given by rental contract to several persons, the party who cause the registration of the agreement

የቀደምትነት መብት ያገኛል። ሁሉም ያላስመዘገቡ ሆነው በሚገኙበት ጊዜ በመሬቱ መጠቀም የጀመረው ወገን የቀደምትነት መብት ይኖረዋል።

8. ማናቸውም የኪራይ ውል ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ተፈፃሚነቱ አከራዩን ብቻ ሣይሆን ወራሾቹንም ሆነ በመሬቱ ላይ መብት ያላቸውን ሌሎች ወገኖች ጭምር የሚያስገድድ ይሆናል።

9. ተከራይ መሬቱን ባግባቡ ካለመያዙ የተነሣ አከራይ በሚመለከተው የመንግሥት አካል አማካኝነት ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ወይም ቅጣት የተወሰነበት እንደሆነ አከራይ የተወሰነው ጊዜ ከማብቃቱ በፊት የኪራይ ውሉን በተናጠል እንዲያፈርስ በቂ ምክንያት ይሆነዋል።

10. ውሉን ለማፍረስ በቂ ምክንያት አለኝ የሚል ማንኛውም ወገን የውል ይፍረስልኝ አቤቱታውን ከማቅረቡ በፊት ውሉን ማፍረስ እንደሚፈልግ ገልፆ በቅድሚያ የስድስት ወር የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ለሌላው ወገን መስጠት አለበት።

## 13. ?? ? ?? ?? ??? ? ? ?? ?? ? ?? ? ?? ??? ? ?? ? ?? ?????? ?? ? ??? ? ??

1. በአዋጁ አንቀጽ 19 ስር በተደነገገው መሠረት በሊዝ የተገኘ በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የዕዳ ዋስትና ሆኖ በሚያዝበት ወቅት ባለዕዳው በስምምነቱ በተገለፀው የጊዜ ገደብ

first shall have prior right. Where it is found that none of them cause the registration, the person who has started to use on the land shall have the prior right.

8. Where any rental contract is effected, its application shall enforce not only the lessee but the heirs and those other parties who may have the right on the land holding.

9. Where the lessee is given a warning or determined on a penalty by the concerned Government body due to that he does not properly manage the land, this hall be justifiable reason to the lessor to invalidate the rental contract individually before the termination of its definite time.

10. Any party who has a good reason for invalidating the contract, before he submits his appeal of invalidating contract, he shall give a six-month written warning in advance to another party indicating that he wants to invalidate the contract.

## 13. The Rights of Creditor where a mortgage of Rural Land use Right obtained through Lease

1. Pursuant to the provision of Art 19 of the proclamation, where rural land use right is secured in mortgage if the borrower does not pay within definite period of time in

ውስጥ ያልከፈለ እንደሆነ ባለገንዘቡ አንድ ወር የቅድሚያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ ያለተጨማሪ ስነ-ስርዓት ለባለስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት በማመልከት አግባብ ባለው ቀበሌ አስተዳደር አስፈፃሚነት በመሬቱ ላይ ያለውን ሀብት ሊረከብ ወይም መሬቱን በስምምነታቸው ውስጥ በተደነገገው መሠረትና ለተወሰደበት የሊዝ ዘመን ራሱ ሊጠቀምበት ወይም ለሌላ ሰው አከራይቶ ገቢውን ሊቀበልበት ይችላል። ይህ ድንጋጌ በተመሳሳይ መልኩ በይዞታቸው ላይ የለማ ንብረትን በመያዣነት ላስያዙ ሌሎች ባለይዞታዎችም ተፈሚ ይሆናል።

accordance with the agreement, the creditor may, having given a month written notice without any extra procedure by applying to the Authority's woreda representative office through the execution of respective kebele, receive the asset on the land or use the land in accordance with the provision of their agreement and for the determined period of lease or rent same to another person and receive the revenue. This provision shall apply on the other holders who secure their property developed on their holding by a mortgage mutatis –mutandis.

## 14. ?? ?? ??? ? ?? ??? ? ? ?? ???

1. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ተረጋግጦ የተሰጠ የገጠር መሬት ይዞታ መብት ከዚህ በታች በተመለከቱት ምክንያቶች በአንዱ ወይም በሌላው ሊታጣ ይችላል፡-
   ሀ/ በዝቅተኛ መነሻ ደመወዝነት እንዲከፈል በመንግሥት ከተወሰነው አማካይ የወር ደመወዝ መጠን ያላነሰ ገቢ በሚያስገኝ ቋሚ ስራ ላይ ተቀጥሮ መገኘት፤
   ለ/ ከግብርና ሥራ ውጭ በሆነና ግብር በሚያስከፍል የሥራ መስክ ተሰማርቶ መገኘት፣
   ሐ/ ያሉበትን ሣያሳውቁ ወይም መሬቱን ሣያከራዩ ወይም ይህንኑ በሀላፊነት የሚያስተዳድር ሰው ሣይወክሉ ተከታታይነት ካላቸው አምስት

## 14. Conditions of deprivation of the Rights of Land Holdings

1. Rural land holding rights given in accordance with the proclamation and this regulation hereof, may be deprived of with one or other reasons indicated hereunder:
   A. Be employed in a permanent job which may be earned an income not less than average monthly salary determined by the government to be paid in minimum starting salary;
   B. be engaged in work field other than agricultural activity and excisable one;
   C. be vanished for five consecutive years without notifying his present address or not renting his land or not representing a person who may administer such a

አመታት በላይ ከመኖሪያ አካባቢ መጥፋት፤

መ/ ያለበቂና ትክክለኛ ምክንያት ወይም ከሚመለከተው ቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ወይም ይኸው ከሚታቀፍበት የባለስልጣኑ ወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት በቅድሚያ የፅሁፍ ፈቃድ ሣያገኙ ተከታታይነት ካላቸው ሶስት ዓመታት በላይ መሬቱን ጦም ማሣደር፤

ሠ/ በይዞታው ስር ያለን መሬት መንከባከብ እየተቻለ በውሀ መሸርሸር ክፉኛ እንዲጎዳ ወይም አካባቢው እንዲጎሳቆል አድርጎ መገኘት፤

ረ/ የይዞታ መብቱን ፈቅዶ ስለመተው በፅሁፍ ማሣወቅ፤

ሰ/ መሬቱ ለህዝብ አገልግሎትይውል ዘንድ አግባብ ባለው አካል የሚተላለፍ ውሣኔ።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተመለከተው ድንጋጌ የገቢው መጠን የቱንም ያህል ቢሆን ከጡረታ በሚያገኘው ገቢ በሚተዳደር ወይም ለብሔራዊ አገልግሎት በተመደበ በማናቸውም ሰው ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር ሐ ወይም መ ድንጋጌዎች ስር እንደተመለከተው ከመኖሪያ አካባቢው የጠፋ ማንኛውም ሰው መጥፋቱ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ ሶስት ዓመት የሞላው ወይም መሬቱ በተለያዩ ምክንያቶች ያለፈቃድ ጦም ካደረበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት የሞላው

responsibility;

D. allow the land to lie fallow for three consecutive years without an adequate and right reason or without having a prior written permit from pertinent kebele Land Administration and use committee or form the Authority's of woreda; representative office:

E. cause severe degradation of the land under his holding by flood erosion where there is the opportunity to protect it or the impoverishment of the environment;

F. notifying in writing that he has willingly given up his holding rights;

G. on decision passed by pertinent body with the view to using the land for public service.

2. The provision stipulated under sub. Art 1 of this Article hereof, shall not be applicable to any person who lives on a retirement pension or is assigned to national service no matter how much his income is

3. A person who has vanished without trace form his residing locality, as it is stipulated under the provisions of sub. art 1 letter C and D of this Article hereof, where it ensured that it has completed three years since his disappearance or it has completed two years since his land has lied fallow without permit

መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ጠፍቷል የሚሰኝበት የአምስት ዓመት ጊዜ ገደብ እስኪደርስ ወይም ባለይዞታው መሬቱን ጥቅም ላይ እንደሚያውል እስከታመነ ድረስ የይዞታ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ መሬቱ በቀበሌው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ስር እየተዳደረ ለጊዜው መሬት የሌላቸው ሰዎች ሲጠቀሙበት እንዲቆዩ ሊወሰን ይችላል።

4. ከዚህ በላይ በተደነገገው መሠረት መሬቱ በቀበሌው ስር እንዲተዳደርና ለሌሎች ሠዎች ተሰጥቶ ለጊዜው ጥቅም ላይ እንዲውል ሲወሰን በመሬቱ ላይ ያረፈ የባለይዞታው ሀብት ቢኖር ይህንኑ እንዳይጎዳ በሚገባ የመንከባከብና በባለአደራነት የመጠበቁ ሀላፊነት የቀበሌው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ይሆናል።
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሠ እና ረ ድንጋጌዎች መሠረት የመሬት ይዞታ መብቱን ያጣ ማንኛውም ሰው መሬቱን ከማስረከቡ በፊት በራሱ ጥፋት ምክንያት በዚሁ መሬት ወይም በአካባቢው ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ይህንኑ ከማስተካከል ሀላፊነት ነፃ አይሆንም።
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር በሰፈሩት ምክንያቶች የመሬት ይዞታ መብቱን ያጣ ማንኛውም ሰው እንደተገቢነቱ በመሬቱ ላይ ያፈራውን ንብረት አንስቶ የመውሰድ፣ አንስቶ ሊወስደው ለማይችለው ወይም

due to various reasons, without prejudice to his holding rights, the land, being administered under the kebele land administration and use committee, may be determined that those who have no land may use it until the time limit of five years is complete to say that he is vanished without trace or it is believed that he may use the land.

4. Where it is decided that the land is to be administered under the kebele and temporarily given to other persons to be used, the holder's asset on the land if any, the reasonability of taking care of properly and protecting same not to be harmed and damaged shall be the kebele land administration and use committee.
5. Any person who has deprived of his right of land holding in accordance with the provisions of letter No. of E and F of sub. Art. 1 of this Article hereof, where it is ensured that he has caused damage on this land or the environment due to his fault before he has submitted the land, he shall not be free form responsibility of maintaining this hereon.
6. A person who is deprived of his land holding rights due to the provisions stipulated under sub-Art. 1 of this Article hereof, as deemed appropriate, shall have the rights to lift assets he produced on his land if he could not lift it

እንዳይወስድ ለተደረገው ንብረት ደግሞ ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ የማግኘትና የመሬቱን ለምነት ጠብቆ ለማቆየት ያወጣውን ወጪ የማስመለስ መብት ይኖረዋል።

or is made not to be lifted the asset, to obtain reasonable compensate beforehand and to return the cost he has expended in order to maintain fertility of the land.

## 15. ? ? ?? ? ? ? ?? ? ? ? ? ??? ??? ? ? ?

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ /7/ መሠረት የክልሉ መንግሥት በሚያዘጋጀው የሰፈራ ፕሮግራም በፈቃደኝነት ተሣትፎና ትክ መሬት ተሰጥቶት ማምረት የጀመረና ምርጫው በሰፈረበት አካባቢ ለመኖር መሆኑን በጽሁፍ ያረጋገጠ ማንኛውም አርሶ አደር ነባር ይዞታውን ለቀበሌው መሬት አስተዳደር አጠቃቀም ኮሚቴ ያስረክባል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለአካባቢ ጥበቃ፣ ለተፈጥሮ ሀብት ልማትና ለዘላቂ ምርታማነት ሲባል ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ የሚደረግ የህዝብ እንቅስቃሴ አካል ሆኖ በአዲሱ አካባቢ ለምርት አገልግሎት የሚውል ተመሣሣይ መሬት የሚሰጠው ማንኛውም ሰው ነባር ይዞታውን ለሚመለከተው የቀበሌው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ የመመለስ ሃላፊነት ይኖርበታል።

## 15. Effects of Obtaining surrogate Land Holding

1. pursuant to sub-Art.7 of Art.5 of this regulation hereof, any farmer who has willingly participated in the resettlement programme the Regional State may formulate and having been given a replacing land and commenced to produce harvest and ensured in writing that he has preferred to live in the area thereon he resettled shall submit his former holding to the kebele land Administration use committee. Particulars shall be determined by a directive

2. Without prejudice to the provision of sub. Art. 1 of this Art. hereof, any person who has been given same land to be used for production service in the new area shall have a responsibility to return his former holding to the respective kebele land administration and use committee being a part of public movement made from one area to another area for the sake of environment protection, natural resource development and long-lasting productivity.

# ክፍል አራት

# ከገጠር መሬት ይዞታና አጠቃቀም ስለሚመነጩ ግዴታዎች

## 16. ?? ?? ?????? ?????

1. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት የገጠር መሬት ይዞታ ወይም በዚሁ የመጠቀም መብት ያገኘ ማንኛውም ሰው ከዚህ በታች የተመለከቱት ግዴታዎች ይኖሩበታል።
   ሀ/ በይዞታ ወይም በኪራይ የተሰጠውን መሬት በአግባቡ የመንከባከብና አስቀድመ የተዘጋጀ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በሚኖርበት ጊዜ ደግሞ በዚሁ ዕቅድ መሠረት የመጠቀም፤
   ለ/ በመሬቱ ላይ ያለማውን ሰብል በአካባቢው ከፍተኛ ጉዳት ከሚደርሱ አረሞችና ተዛማጅ ፀረ ሰብል ተባዮች የመጠበቅ፣
   ሐ/ ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ በሰብሉ ወይም በመሬቱ እንዲሁም በአጐራባች ማሳዎች ላይ ጉዳት የማያደርሱ ዛፎችን በመሬቱ አካባቢ የመትከልና ተንከባክቦ የማሳደግ፤
   መ/በሰውም ሆነ በንብረት ላይ ጉዳት በማያደርሱና በአካባቢው ተጠልለው በሚኖሩ የዱር እንስሳት ላይ ሆነ ብሎ ጥቃት አለመፈፀም፣ ጉዳት ያደርሳሉ ተብለው በሚገመቱት ላይ ደግሞ ይህንኑ ለመከላከል የሚያስችል እርምጃ ከመውሰድ በፊት አግባብ ካለው አካል ፈቃድ የመጠየቅ፣

# PART FOUR

# OBLIGATIONS EMANATED FROM RURAL LAND HOLDING AND UTILIZATION.

## 16. Obligations of the Land Users

1. A person who has acquired rural land holding or the use rights on this shall, pursuant to the proclamation and this regulation hereof, have obligations indicated hereunder:
   A. to properly protect the land granted to him either in holding or in a rent and where there is land use plan beforehand prepared, use his land in accordance with this plan;
   B. to protect the crops he has developed on his land from weeds which may cause severe damage in the area and same anti-crop pests;
   C. with the details to be determined by a directive, to plant trees which do not cause harm on the crop or his land as well as on the plots of neighboring land surrounding his land and take care of them.;
   D. not deliberately to do violence to wild animals which do not cause damage on human beings or property and sheltered themselves in the area; but to those wild animals which may cause damage, before an action that enable to prevent this is to be taken, to request a permit from an appropriate body;

ሠ/ ከአጐራባች ይዞታዎች ጋር የሚጋሩትን ድንበር ያለማፍረስ፤

ረ/ የወል መሬቶችን ወሰን ያለመጋፋት፤

ሰ/ አግባብ ባለው አካል የተከለሉ መንገዶችን ያለመዝጋት፤

ሸ/ መልካዓ ምድራዊ አቀማመጡ ምክንያት ከላይኛው አካባቢ በመነሳት የተፈጥሮ አቅጣጫውን ተከትሎ የሚፈሰውን ውሃ በመቀበል ወደታች እንዲያለፍ የማድረግ፤

ቀ/ በመሬቱ ላይ የሚፈሰው ውሀ ወደታች እንዲያልፍ በሚያደርግበት ጊዜ አላግባብ የውሃውን የተፈጥሮ ፍሰት አቅጣጫ በመቀየር የታችኛው መሬት የውሃ ጫና እንዲያርፍበት ያለማድረግ፤

በ/ ማናቸውም አካል አማካኝነት የመስኖ ልማት ሥራ በሚከናወንበት ጊዜ የመስኖ መስመሩ በመሬቱ ላይ የሚያልፍ መሆኑ የታወቀ እንደሆነ ይህንኑ ያለመከልከል፤

ተ/ በመሬቱ ላይ የእሳት ቃጠሎ እንዳይነሣ ተገቢው ሆኖ የተገኘውን የጥንቃቄ እርምጃ የመውሰድ፤

ቸ/ አግባብ ባለው አካል መሬቱ እንዲለካ ወይም የቅየሳ ሥራ እንዲካሄድበት ሲጠየቅ በቅርብ የመተባበር፤

ኀ/ ለራሱ፣ ለቤተሰቡም ሆነ ለሌሎች ባለይዞታዎች አጠቃቀም ይረዳ ዘንድ እንዳስፈላጊነቱ በመሬቱ ዳር ወይም ውስጥ በቂና ሰፋት ያለው መተላለፊያ መንገድ የመፍቀድ፤

E. not to cross the borderline which may be shared with the nearby holdings;

F. not to cross the borderlines of communal lands;

G. not to close roads demarcated by an appropriate body;

H. take and to cause downward passage of water which may flow following its natural course by starting from higher area due to its topography;

I. where the water that may flow on his land cause to pass downward, not to cause the lie of water load on the land below it by improper diversion of the direction of natural course of the water;

J. where an irrigation development activity is being undertaken by any body and it is known that the irrigation line may pass through his land thereon, not to forbid this;

K. to take an appropriate safety measure not to break out fire on his land;

L. to closely cooperate where he is asked by a pertinent body with the view to measuring his land or undertaking a surveying activity.

M. to allow sufficient and wide passageway, as deemed necessary, on the border of his land or through it with the view to helping the use of himself, his family as well as other holders;

ነ/ በሌሎች ባለይዞታዎች ወሰን ውስጥ ሲያልፍ ንብረታቸው እንዳይጐዳ ጥንቃቄ የማድረግ፤

ኘ/ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በሚሰጥበት ጊዜ ይህንኑ ተከታትሎ የማውጣት።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር /ሀ/ስር የተመለከተው መሬትን የመንከባከብ ሀላፊነት የሚከተሉትን ዝርዝር ተግባራት ያጠቃልላል:-

ሀ/ በአካባቢው ባህል በተለመደው መሠረት መሬቱን ማረስና ዘመናዊ የመሬት አጠቃቀም ዘዴን በተመለከተ ደግሞ በሚሰጠው የባለሙያ ምክር አገልግሎት መጠቀም፤

ለ/ የአፈርና የውሀ ጥበቃ ሰራን ማከናወንና

ሐ/ በሰብሉም ሆነ በአካባቢው ላይ ጉዳት የማያደርሱ ዛፎችን ፈቃድ ሳያገኙ ከመቁረጥ መቆጠብ።

3. መሬቱ በወንዝ ዳር ወይም ገደላማ በሆነ አካባቢ የሚገኝ ማንኛውም ባለይዞታ ባለስልጣኑ ይህንኑ ደንብ ተከትሎ ወደፊት በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው ርቀት መጠን ከወንዙ ወይም ከገደሉ አርቆ የማረስና ያልታረሰውን የወንዙን ዳር አካባቢ በይዞታው ስር አድርጐ እየተካ የሚጠቀምበት ዛፍ የማልማት ግዴታ አለበት።

N. wherever he passes through other holdings' borderline, to take care of their property not to be harmed;

O. where land holding certificate book is issued, to pursue and take such a certificate.

**2.** The responsibility of land protection indicated under the provision of sub. Art.1 (A) of this Article hereof, shall comprise the following specific duties:

A. to plow his land in accordance with customary local practice and as regards modern land use method, use a professional counseling service given to him;

B. to undertake activities of soil and water protection and;

C. to abstain from cutting trees which do not cause harm on the crops and the environment thereon, Without having a permit.

**3.** Any holder whose lands is found near to a bank of a river or gully area, shall have an obligation to plow his land far away form the river or the gully a distance determined by a directive that may be issued by the Authority subsequent to this regulation and, having made the untilled area of river bank land under his holding, grow a tree that he may use in substitute.

4. የመሬት ተጠቃሚ ድርጅቶችም ሆኑ አልሚ ባለሀብቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር ከሠፈሩት ግዴታዎች በተጨማሪ የመሬት አጠቃቀም ፕላን በማዘጋጀትና ለባለስልጣኑ አቅርበው የማስፀደቅ ሀላፊነት አለባቸው።

## 17. ? ? ? ? ??? ??? ??? ???? ?? ? ? ?

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 16 ስር የተደነገገውን የትኛውንም ግዴታ ያላከበረ ማንኛውም የመሬት ባለይዞታ ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ እንደቅደም ተከተሉ የቃል ወይም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።
2. በተሰጠው የቃል ወይም የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መሠረት ጥፋተኛው ከስህተቱ ሊታረም ያልቻለ እንደሆነ እንደጥፋቱ አይነትና ደረጃ ከዚህ በታች የተመለከቱት አስተዳደራዊ እርምጃዎች ሊወሰዱበት ይችላሉ:-

ሀ/ በአንድ አይነት ጥፋት የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ካገኘበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠሩት ሁለት ዓመታት ውስጥ ያንኑ ጥፋቱ በተመሣሣይ ሁኔታ ደግሞ የተገኘ እንደሆነ መሬቱን ተነጥቆና የመጠቀም መብቱ ለአምስት ዓመታት ያህል ታግዶ የመንከባከብ ግዴታን ለሚገባ ለሌላ ሰው በኪራይ እንዲሰጥና ጥቅም ላይ እንዲውል

4. Land user organizations and developers shall, besides the obligations stipulated under sub. Art 1 of this Article hereof, have the duty to prepare and submit land use plan to the Authority and have got its approval.

## 17. Effects of Non-performance of Obligation

1. Any land holder who has failed to respect any obligation provided under sub-Art 16 of this regulation shall, with the details to be determined by a directive, be given oral or written notice respectively.
2. Where the offender might not be corrected from his fault, in accordance with the oral or written notice given to him, administrative measures indicated herein under may be taken up on him, as the type and level of his offence.

A. where he is found that he has committed again such an offence in a similar condition within two years since he has received a final notice in one type of offence, his land is taken away and his use right is deprived of for five years, it may be determined by the pertinent Authority's woreda representative office that the land to be given in rent and used to another person who may enter into an

በሚመለከተው የባለስልጣኑ ወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት ሊወስን ይችላል።

ለ/ ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ቁጥር ሀ ስር የተመለከተው እርምጃ ተፈፃሚ ከሆነበት በኋላ ጥፋተኛው መሬቱን ከተከራዩ መልሶ ከተቀበለበት ቀን አንስቶ በሚቆጠሩት ሌሎች ሁለት አመታት ውስጥ ያንኑ ጥፋት እንደገና መፈፀሙ የተረጋገጠበት እንደሆነ በመሬት የመጠቀምና ገቢ የማግኘት መብቱ ለተከታዩቹ አምስት አመታት ታግዶ ይቆያል በዚህ የማይታረም መሆኑ ከታወቀ ደግሞ ምትክ ቦታ ካለማግኘቱ በተጨማሪ በመሬቱ ላይ እስከዚያው ጊዜ ድረስ ላደረገው ቋሚ ማሻሻያና ላለማው ንብረት ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ ተከፍሎት ይዞታውን ከነአካቴው እንዲለቅ አግባብ ባለው የባለስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት ሊወሰንበት ይችላል። ሆኖም ይህ አይነቱ ውሣኔ የተላለፈበት ማንኛውም ሰው ውሣኔውን በጽሁፍ ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ በሰላሣ ቀናት ውስጥ ለወረዳው ፍ/ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው።

3. ማንኛውም የመሬት ተጠቃሚ የሚጋራውን የወል መሬት የመንከባከብ ችሎታ እያለው አልተባበርም ያለ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር በተደነገገው መሠረት እንደ ቅደም ተከተሉ የቃል ወይም የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

obligation of protection the land.

B. after the measure provided under letter no. A herein above has been applied to him, where the offender is ascertained that he has committed again such an offence within two years since he has regained the land from the lessee, his rights of land and obtaining an income shall be deprived of for consecutive five years. If it is known that he is not corrected by this, besides he never acquires surrogate land, having been beforehand paid commensurate compensation for the permanent improvement he has made and property he has developed on is land until then, it may be decided up on him to be expropriated from his holding forever by the pertinent Authority's woreda representative office; of Provided, however, that any person to whom such a decision is made his right of appeal to the woreda court within thirty days from the date of receiving the decision in writing shall be respected.

**3.** Where any land user who has failed to cooperate in protecting communal land, but has the capacity to do so, he shall, pursuant to the provision of sub. Art 1 of this Article hereof, be given oral or written notice respectively.

4. ጥፋተኛው የመጨረሻ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ካገኘበት ቀን አንስቶ በሚቆጠሩት አምስት አመታት ውስጥ ያንኑ ጥፋት በተመሣሣይ ሁኔታ ደግሞ የተገኘ እንደሆነ ከአንድ አመት ለማይበልጥ ጊዜ የወል መሬቱ ተጠቃሚ እንዳይሆን በባለስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት ሊታገድና በዚሁ ሳይታረም ቀርቶ በተከታታይ ለሶስተኛ ጊዜ ካጠፋ ለዘለቄታው የወል መሬቱን እንዳይጠቀም ሊወሰንበት ይችላል።

4. Where the offender has committed again such an offence in the same way within five years since he has received a final written notice, having been deprived of his right not to use the communal land by the Authority's woreda representative office and if he did not correct his mistakes upon this penalty, and consecutively committed offence for the third time, it may be decided upon him totally not to use the communal land forever.

## 18. ?? ??? ???? ?????? ???? ?? ????

1. በዚህ ደንብ መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ ማንኛውም የመሬት ባለይዞታ የቃል ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኋላ የመጀመሪያ ደረጃ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ሊደርሰው የሚችለው ቢያንስ በአንድ የሰብል ዘመን ልዩነት ይሆናል።
2. በዚህ ደንብ መሠረት የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የሚሰጠው በጠቅላላው ሶስት ጊዜ ሆኖ እያንዳንዱ ማስጠንቀቂያ በአንድ የሰብል ዘመን ልዩነት መሰጠት ይኖርበታል።
3. የቃል ማስጠንቀቂያም ሆነ የመጀመሪያ ደረጃ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የሚሰጠው አግባብ ባለው የቀበሌ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ አማካኝነት ሲሆን ሁለተኛና ሶስተኛ ደረጃ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያዎች በሚመለከተው የባለስልጣኑ ወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት በኩል

## 18. Procedures of Giving Oral and Written Warnings

1. A preliminary written warning may be communicated to any land holder who has failed to discharge his obligations pursuant to this regulation hereof, after he has been given oral warning, shall be at least in a different harvesting year.
2. Pursuant to this regulation hereof, the written warning is to be given totally three times and each warning shall have to be given in a different harvesting year.
3. Oral warning and preliminary written warning are to be given by the appropriate kebele Land Administrative and use committee, but second and third level written warnings shall be given through the pertinent Authority's woreda representative office.

ይሠጣሉ።

4. በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ቁጥር ሀ እና ለ ድንጋጌዎች መሠረት በመሬት የመጠቀም መብቱ ለጊዜው የታገደበት ማንኛውም ሰው መብቱ ከታገደበት ከአንድ አመት ቆይታ በኋላ እገዳው ቢነሳለት መሬቱን እንደሚንከባከብ ግዴታ ገብቶ ውሣኔውን ለሰጠው ለባለስልጣኑ መ/ቤት እገዳው እንዲነሣለት ሊያመለክት ይችላል።

4. Any person whose use right on the land is temporarily suspended may, pursuant to the provisions of sub. Art.2, letter no. A and B of Art. 17 of this regulation hereof, having been entered into an obligation that he may conserve his land if the ban is reinstated, apply to the office of the Authority who gives the decision for the reinstatement of the ban after 1 year duration since his right has been suspended.

## ክፍል አምስት
## መሬትን ስለመለካትና ስለይዞታ ማረጋገጫ ደብተር

## PART FIVE
## MEASURING LAND AND HOLDING CERTIFICATE BOOK

### 19. ? ??? ??? ???

1. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ለመሬት ተጠቃሚዎች በይዞታነት የተሰጠ፣ ማህበረሰቡ በወል የያዘው ወይም በመንግሥታዊ፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና የሀይማኖት ተቋማት ስር ያለ እያንዳንዱ የገጠር መሬት በባለስልጣኑ አማካኝነት በዘመናዊ ወይም በባህላዊ መሳሪያ ተለክቶ ድንበር የሚያሳይ ምልክት ይደረግበታል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት የተለካው መሬት አቅም በፈቀደ መጠን የእያንዳንዱን ባለይዞታ ድንበር

### 19. Measuring Land

1. Each rural land which is granted to users in holding, communally held by the community or non-governmental organizations, pursuant to the proclamation and this regulation hereof, having been measured by the Authority in traditional or modern tools, a landmark indicating the boundary shall be put up thereon.
2. The land which is measured, in accordance with the provision of sub. Art. 1 of this Article hereof, to such an extent that allows a capacity,

ለይቶ የሚያሳይ ካርታ ይዘጋጅለታል።

3. መሬቱ የሚለካ ማንኛውም ባለይዞታ የመለካቱ ሥራ ሲካሄድ በቦታው መገኘት ይችል ዘንድ እንዳመችነቱ በህዝባዊ ስብሰባ ወይም በግል እንዲነገረው ይደረጋል።

4. መሬቱ ሲለካ እንዲገኝ በአግባቡ ጥሪ ደርሶት ለመገኘት ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው የድንበር መለካቱ ሥራ በሌለበት ይካሄድ ዘንድ ሙሉ በሙሉ እንደተስማማ ይቆጠራል።

5. የተዋሳኝ መሬቶች ድንበር በተቻለ መጠን በአዋሳኝ ባለይዞታዎች የጋራ ስምምነት መወሰን ይኖርበታል። ድንበሩን በአዋሳኝ ባለይዞታዎች ስምምነት መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ አግባብ ያለው ቀበሌ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ በአካባቢው ሽማግሌዎች አስተያየት ተደግፎ ለጉዳዩ የመጨረሻ እልባት ይሰጣል።

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ስር የሠፈረው ድንጋጌ ቢኖርም በመሬት አለካኩም ሆነ በድንበሩ አወሳሰን ቅር የተሰኘ ማንኛውም ባለይዞታ የቅሬታውን ምክንያት በዝርዝር ገልፆ ልኬታው እንደገና እንዲከናወንለትና ድንበሩ እንዲወሰንለት መሬቱ ከተለካበት ቀን ቀጥሎ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት ሊያመለክት ይችላል። አቤቱታው የቀረበለት

a map which identifies and indicates the boundary of each holder shall be prepared thereof.

**3.** Any land holder whose land may be measured is made to be told in public meeting or in person, as it is favorable, with the view to appearing therein where the work of measuring is being undertaking.

**4.** Any person who properly receives a call to be shown up when his land is being measured and failed to appear therein, it shall be regarded as he fully consents that the boundary measuring work is to be undertaken in his absence.

**5.** The boundary of adjacent lands shall be, as much as possible, demarcated in common consent of adjacent holders. Where it is impossible to decide the boundary in the agreement of adjacent holders, the pertinent kebele land administration and use committee shall, being supported by the recommendation of local elders, give final resolution.

**6.** Notwithstanding the provision stipulated under sub. Art. 5 of this Article hereof, any holder who complains regarding the land measurement and demarcation of the boundary may, stating reasons of his complaints in detail, apply to the Authority's woreda representative office in order to be undertaken the measurement again and then be demarcated the boundary within 15 days after the land is measured. The Authority representative office

የባለስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤትም ጉዳዩ በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ ወስኖ ምላሹን ለአቤቱታ አቅራቢው በፅሁፍ መስጠት ይኖርበታል።

7. መሬቱ ከተላከ በኋላ በውሃ በመሸርሸሩ፣ በጐርፍ በመወሰዱ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ በሌላ በማናቸውም ምክንያት መጠኑ በከፍተኛ ደረጃ እንደተለወጠ የሚያሳዩ ተጨባጭ መረጃዎች የተገኙ እንደሆነ ወይም ለተለያዩ ሰዎች በመከፋፈሉ የባለይዞታዎች ቁጥር ለውጥ ካጋጠመ መሬቱ እንደገና ሊለካና አዲስ ካርታ ሊዘጋጅለት ይችላል።

## 20. ?? ? ?? ??? ? ???? ????

1. ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ የባለስልጣኑ ወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ፎቶ ግራፉ ተለጥፎበት በስሙ የሚዘጋጀውን የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር መጠየቅና ማውጣት አለበት።
2. መሬቱ ባልና ሚስት በአንድነት ወይም ሌሎች ሠዎች በጋራ የያዙት መሆኑ የታወቀ እንደሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በሁሉም የጋራ ባለይዞታዎች ይዘጋጃል።
3. ተቃራኒ የፅሁፍ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር ባልና ሚስት የሚጠቀሙበት መሬት እኩል በሆነ መጠን የሚጋሩት ይዞታ እንደሆነ ይወሰዳል።

of woreda shall, deciding the matter within 15 days, reply the answer to the complainer in writing.

**7.** After the land has been measured, where there is tangible information that indicates the area of land is highly changed due to eroded by water, washed away by flood or by any other reason or it is redistributed to various persons and occurred a change of numbers of holders, the land may be re-measured and a new map is prepared thereof.

## 20. Land Holding Certificate Book

**1.** Any rural land holder shall request and issue land holding certificate may be prepared in his name and attached a photo thereon in accordance with time table the Authority's woreda representative office may set out.

**2.** Where it is ascertained that the land is held together by spouses or by other persons in common, the holding certificate shall be prepared in both common holders.

**3.** The land which is used by a husband and a wife shall, unless a contradictory written document is submitted, be regarded as it may be equally shared holding.

4. ይህንኑ የሚቃረን ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስሙ ተዘጋጅቶ የተሰጠው ማንኛውም ሰው በአዋጁና በዚሁ ደንብ መሠረት የመሬቱ ትክክለኛ ባለይዞታ ተደርጐ ይቆጠራል።

5. ባልና ሚስት በአንድነት የያዙትን መሬት በተመለከተ ሀሰተኛ መረጃ ለባለስልጣኑ በመስጠት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩን በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ ማውጣት ስሙ በደብተሩ ውስጥ ያልተጠቀሰውን በምዝገባ ወቅት የነበረውን የትዳር ጓደኛ የይዞታ መብት የማሳጣት ውጤት አይኖረውም።

6. የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በአንደኛው ስም ተዘጋጅቶ ከተሰጠ በኋላ ጋብቻ የተፈፀመ እንደሆነ ተጋቢዎች ይህንኑ ፍሬ ነገር አግባብ ላለው የቀበሌ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ በወቅቱ ገልፀው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ ተሻሽሎና በሁለቱም ስም ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው ማመልከት ይችላሉ።

7. የመሬት ይዞታው በየትኛውም ህጋዊ ይዞታ ከአንዱ ወደ ሌላው በሚተላለፍበት ጊዜ ወዲያውኑ መሬቱ ለሚገኝበት ቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ቀርቦ በማመልከት በአዲሱ ባለይዞታ ስም ተለዋጭ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ማውጣት ግዴታ ይሆናል።

**4.** Any person who is granted land holding certificated book having been prepared in his name shall, unless the evidence which contradicts this is submitted pursuant to the proclamation and this regulation hereof, be considered as an appropriate apposite legal holder.

**5.** As regards the land a husband and a wife held together, issuing the holding certificated book only in the name of one spouse by submitting a false document to the Authority and depriving of right of the spouse whose name is not listed in the certificate book but he was present during registration shall be invalid.

**6.** Where a marriage is concluded after the land holding certificate book has been prepared and granted in the name of one spouse, the spouses may apply to the respective Kebele Land Administration and Use Committee, timely stating this core of matter with the view to granting to them the holding certificate book having been amended and prepared in the name of both of them.

**7.** Where the land holding is transferred from one person to another in any legal holding, it shall be an obligatory to issue substitute holding certificate book in the name new holder by applying in person to the respective kebele land administration and use committee forthwith.

8. የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በማናቸውም ሁኔታ ሲጠፋ፣ ሲቀደድ ወይም ሲበላሽ ይኸው ሁኔታ እንደታወቀ አግባብ ላለው የቀበሌ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ በማመልከት ይህንኑ ደንብ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ የሚወስነውን የአገልገሎት ክፍያ ፈፅሞ እንደገና ማውጣት አስፈላጊ ይሆናል።

**8.** Where the land holding certificate book is lost, torn or spoiled, it shall be necessary to reissue same, having paid the service charge determined by a directive may be issued subsequent to this regulation by applying to the pertinent Kebele Land Administration and Use Committee as soon as such an incidence is known.

## 21. ?? ?? ??? ? ???? ???? ??? ???? ?????

በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ተዘጋጅቶ የሚሰጥ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ከዚህ በታች የተመለከቱትን ዝርዝሮች መያዝ አለበት:-

ሀ/ የመሬቱ ባለይዞታ /ዎች/ ሙሉ ስም፣ የመኖሪያ አድራሻና ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣

ለ/ የባለይዞታው ባለይዞታዎች ዋና ዋና መብቶችና ግዴታዎች በአጭሩ፣

ሐ/ የመሬቱ መለያ ቁጥርና የይዞታው ስፋት፤

መ/ የደብተሩ ተራ ቁጥር፤

ሠ/ መሬቱ የሚሰጠው የአገልግሎት አይነት፤

ረ/ መሬቱ የሚገኝበት የለምነት ደረጃ፤

ሰ/ ደብተሩ የተሰጠበት ቀን፣ ወርና አመተምህረት፤ እና

ሸ/ ሰነዱን ያዘጋጀው ሠራተኛና ያረጋገጠው ሀላፊ ሙሉ ስም፣ ፊርማና ማህተም።

## 21. Details that The Land Holding Certificate book Contains

The land holding certificate book prepared and granted pursuant to the proclamation and this regulation hereof, shall contain particulars/ information indicated herein under:

A. full name, principal address and short photo of holder(s) of the land;

B. major rights and obligations of the holder/ holders;

C. identification number of the land and the area of holding;

D. roll-number of the certificate book;

E. type of service the land is used for;

F. fertility standard of the land;

G. day, month and year of granting the certificate book and;

H. full name and signature of personnel who prepares the document and Head who approves it and seal.

## 22. ??? ? ? ?? ????? ? ??? ??? ?????? ?????

1. የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ከባለስልጣኑ ሳያወጣ በገጠር መሬት ሲጠቀም የተገኘ ማንኛውም ሰው ከዚህ በታች የተመለከቱት አስተዳደራዊ እርምጃዎች ይወሰዱበታል:-

ሀ/ በመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ከቃል ማስጠንቀቂያ ጋር የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ማውጣት እንዳለበት ይነገረዋል፤

ለ/ በቃል ማስጠንቀቂያው መሠረት ካልሠራ በተከታዮቹ ስድስት ወራት ውስጥ ያንኑ የሚያጠናክር የመጀመሪያ ደረጃ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይዞታው ከሚገኝበት ቀበሌ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ በኩል ይደርሰዋል።

ሐ/ በዚሁ ካልታረመ በባለስጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት አማካኝነት በሁለተኛው ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ሁለተኛ ደረጃና በተከታዮቹ ስድስት ወራት ውስጥ ደግሞ ሶስተኛ ደረጃ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያዎች ተዘጋጅተው ይደርሱታል።

መ/ በሶስተኛው ዓመት በመሬት የመጠቀም መብቱ ከአንድ ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ በተጠሪ ጽ/ቤቱ ውሣኔ ታግዶ የሚቆይ ሲሆን በዚሁ እገዳው ወቅት መሬቱን የቀበሌው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ለሌላ ተጠቃሚ ሊያከራየው ይችላል።

## 22. Responsibilities of Using Rural Land without Permission

1. Administrative measures indicated herein under shall be taken on any person who is encountered to use the rural land without issuing land holding certificate book from the Authority.

A. in the first six months, he shall be told that he has to issue a holding certificate book along with oral warning;

B. if he does not perform inline with the oral warning, he shall be given preliminary written warning intensifying such an oral warning through the Kebele Land Administration and Use Committee where the holding is found.

C. Unless he is corrected with this warning, he shall be given second level written warning in the second year of first six months and third level written warning in the following six months through the agent of the Authority's woreda representative of office.

D. in the third year, suspending his use right for not more than one year on the basis of decision of the representative office, the Kebele Land and Administration and Use Committee may rent the land to another user during this suspension.

ሠ/ በአራተኛው ዓመት አግባብ ባለው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ አቤት ባይነት ተጠሪ ጽ/ቤቱ ይዞታውን እንዲለቅና መሬቱን እንዲነጠቅ ሊወስንበት ይችላል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር ሠ ስር የሰፈረው ድንጋጌ ቢኖርም ባለጉዳዩ በአዋጁና በደንቡ መሠረት የተጠየቀውን የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ማውጣት ያልተቻለው በፍትሐብሔር ህግ ውስጥ እንደተተረጐመው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ከዚህ በላይ የተመለከተው መሬት የመነጠቅ ውሣኔ ተፈፃሚ አይሆንበትም።

## 23. ?? ?? ? ?? ?? ? ? ? ? ??? ?? ?? ? ??? ? ?? ?? ? ? ?

1. ይህ ደንብ ከሚፀናበት ቀን ጀምሮ በክልሉ ውስጥ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የሚሰጥበት አነስተኛ የገጠር መሬት ይዞታ መጠን በዝናብ ለሚለማ ማሣ ከ0.25 እና በመስኖ ለሚለማ ማሣ ደግሞ ከ0.11 ሔክታር በታች ሊሆን አይችልም።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ደንቡ ከመፅናቱ አስቀድሞ በነበሩ ይዞታዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 24. ??? ?? ? ???? ?? ?? ????

E. in the fourth year, the representative office may decide on him to expropriate and snatch away his land in an appeal lodged by the appropriate land administration and use committee.

2. Notwithstanding the provision of sub. Art. 1 letter No. F of this Article hereof, where it is ascertained that the subject person is failed to issue holding certificate book requested in accordance with the proclamation and the regulation due to the capacity of beyond one's ability as it is interpreted in civil code the decision of taking away the land shall not be executed on the subject person.

## 23. Area of Minimum Holding of which Holding Certificate Book May be Granted

1. Area of minimum rural land holding that the holding certificate book may be granted may not be less than 0.25 hectares cultivativable by rain and 0.11 hectares cultivativable by irrigation as of the date effective date of this regulation in the Regional State.
2. The provision of sub. Art. 1 of this Article hereof, shall not be applicable to former holdings exist prior to the coming into force of the regulation

## 24. Land Registration and handling of Documents

1. ማናቸውም መሬት እንዴት እንደተገኘ በማን ይዞታ ስር እንዳለ፣ ከማን መሬት ጋር እንደሚዋሰን፣ ደረጃው ምን አይነት እንደሆነ፣ ለምን አገልግሎት እንደሚውልና ምን አይነት ግዴታዎች እንዳሉበት የሚገልፅ መረጃ የያዘ መዝገብ በእያንዳንዱ ቀበሌ የመሬት አስተደደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ጽ/ቤት ተደራጅቶ ይቀመጣል።
2. የመዝገቡ ዋና ቅጅ በሚመለከተው ቀበሌ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ እጅ ሆኖ አንድ ቅጅ በባለስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት ዕጅ ይቀመጣል። የመዝገቡ ማጠቃለያ ለባለስልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት ይላካል። በመዛግብቱ ልዩ ልዩ ቅጅዎች መካከል አለመጣጣም ወይም ቅራኔ የተፈጠረ እንደሆነ በቀበሌው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ዕጅ የሚገኘው መዝገብ የበላይነት ይኖረዋል።
3. መዝገቡን በአንድ መሬት ላይ ህጋዊ መብት ወይም ጥቅም እንዳላቸው ማስረዳት የሚችሉ ሰዎች ሁሉ ጥያቄ ሲያቀርቡ እንዲያዩት ይፈቀድላቸዋል።
4. በመሬት መመዝገቢያ መዝገብ ውስጥ መሬቱ ኪራይን፣ ውርስን ወይም ስጦታን የተመለከተ ግዴታ ያለበት እንደሆነ ይኸው መመዝገብ አለበት። ግዴታው በሚሻሻልበት ወይም በሚያበቃበት ጊዜም መረጃው በዚሁ መሠረት መስተካከል ይኖርበታል።

1. A record containing documents which accounts for any land that how it is acquired, under whose holding it is found, to whose land it is bordered, what kind its standard is, for, what service is used and what kind of obligations it is imposed, shall be organized and kept in each kebele land administration and use committee office.
2. The original record be in the hands of concerned kebele Administration and Use Committee and one copy of it shall be kept in the hand of the Authority's woreda representative office. The summary of the record shall be sent to the Head Office of the Authority. Where a controversy or opposition is aroused over various copies of the record, a record which is kept under the hands of the kebele Land Administration and Use Committee shall have the acceptance over them.
3. Wherever persons who could explain that they may have legal rights or use on a certain land, they shall be permitted to look over the record.
4. Where the land has an obligation with regard to rent, bequeath, or gift in land recording book, such an obligation shall be recorded. Wherever the obligation is to be amended or terminated, the document shall be corrected in line with this alternation.

5. የገጠር መሬት ይዞታን ወይም በዚሁ የመጠቀም መብትና ግዴታን የሚመለከት ማናቸውም ተግባር በአዋጁና በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት በሰነድ መመዝገቢያ መዝገብ ውስጥ ካልገባ በስተቀር በሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሆኖ ሊቀርብባቸው አይችልም።

6. የሰነዱ መዝጋቢ ስምምነቶችን ተቀብሎ ከመመዝገቡ በፊት እያንዳንዱ ሰነድ በትክክል መዘጋጀቱንና የሚመለከታቸው ወገኖች መፈረማቸውን ማረጋገጥ አለበት። በመዝገቡ ውስጥ የተደረገ ማንኛውም ስርዝ ወይም ጭማሪ በመዝጋቢው ፊርማ ካልተረጋገጠ በስተቀር ተቀባይነት አይኖረውም።

7. በሀሰተኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ የተካሔደ የገጠር መሬት ምዝገባ በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ህጋዊ ውጤት አይኖረውም።

8. መዝጋቢው በፈፀመው የአመዘጋገብ ስህተት ምክንያት በማንኛውም ሰው ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ የጉዳቱን ካሣ በመክፈል ረገድ ባለስልጣኑ ሀላፊ ይሆናል። ሆኖም የከፈለውን የጉዳት ካሣ እንዲተካለት ጥፋቱን የፈፀመውን ሰራተኛ በፍትሃብሔር ህግ መሠረት የመጠየቅ መብቱ የተጠቀበ ነው።

## ክፍል ስድስት

## ስለበታች የገጠር መሬት አስተዳደርና

**5.** Any task regarding rural land holding or its use rights and obligations unless it is listed in recording book of a document, pursuant to the provisions of the proclamation and this regulation hereof, it may not be submitted on them as an objection on third parties.

**6.** The registrar of the document, prior to receiving and registering the agreements, shall ensure that each document has been correctly prepared and concerned bodies have signed the document. Any cancellation or inclusion shall not be valid unless it is approved by the registrar’s signature thereon.

**7.** Rural land registration undertaken on the basis of false information shall not have legal effect in accordance with the proclamation and this regulation hereof.

**8.** Where loss is caused on any person due to registration fault made by the registrar, the Authority shall be responsible for with regard to paying the loss compensation; provided, however, that its right to ask of, in civil law, personnel who committed the fault to repay the loss compensation it has paid to the victim shall be respected.

## PART SIX

## አጠቃቀም አካላት ተግባርና ሀላፊነት

## DUTIES AND RESPONSIBILITIES OF HIERARCHICAL LOWER RURAL LAND ADMINISTRATION AND USE BODIES

### 25. ?? ?????? ???? ??? ?/?? ????? ?????

በክልሉ ውስጥ በየትኛውም ወረዳ የተደራጀ የባለስልጣኑ ተጠሪ ጽ/ቤት በአዋጁና በዚህ በደንብ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ሀላፊነቶች ይኖሩታል:-

1. በወረዳው ውስጥ በሚገኙት ቀበሌዎችና ንዑሳን ቀበሌዎች ውስጥ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎችን በብዙሃን ምርጫ፣ ያቋቁማል፣ ሀላፊነታቸውን ስለመወጣታቸውም በቅርብ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
2. የእነዚህኑ ኮሚቴዎች የስራ እንቅስቃሴ የሚያሣይ ሪፖርት በየስድስት ወሩ እያቀረበ በምልዓተ ህዝቡ ያስገመግማል፤
3. ተግባርና ሀላፊነታቸውን አስመልክልቶ ለየኮሚቴ አባላቱ ስልጠና ይሰጣል፣ አቅማቸውን ይገነባል፤

### 25. Duties and Responsibilities of The Authority's Woreda representative Office

The Authority's representative office organized at any Woreda in the Regional State shall, pursuant to the proclamation and this regulation hereof, have the following specific duties and responsibilities:

1. Establish rural land administration and use committees in majority vote in kebeles and sub-kebeles of the Woreda; closely follow up; supervise over the accomplishment of their responsibilities;
2. Having submitted semi-annual reports indicating the activities of these committees, cause the evaluation of same by the entire people;
3. Provide training to the members of the committee regarding their duties and responsibilities; thereby build their capacities;

4. ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን የሚመለከቱ መረጃዎችን በአግባቡ ይይዛል፣ ይጠብቃል፤
5. የመሬት ባለይዞታዎችና ተጠቃሚዎች በህግ የተጣለባቸውን ግዴታ እየተወጡ ስለመሆናቸው ይከታተላል፣ ግዴታቸውን ባልተወጡት ላይ ደግሞ አስተዳደራዊ እርጃዎችን ይወስዳል፤
6. በቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች በተሰጡ የመጀመሪያ ደረጃ አስተዳደራዊ ውሣኔዎች ላይ ቅር የተሰኙ ባለይዞታዎችና ተጠቃሚዎች የሚያቀርቧቸውን አቤቱታዎች ያጣራል፣ የስር ውሣኔዎችን ያሻሽላል፣ ያፀናል፣ ይሽራል፤
7. በወረዳው ውስጥ ያሉና በመንግስት ይዞታ ስር የሚገኙ መሬቶችን መዝግቦ ይይዛል፣ አስተዳደራቸውን ይከታተላል፤
8. ይህንኑ ለማከናወን በወረዳው ውስጥ የተቋቋመ አካል በማይኖርበት ጊዜና ሁኔታ ከገጠር መሬት ጋር የተያያዙ የኪራይ፣ የዋስትና የስጦታና የመሳሰሉ ስምምነቶችን ይመዘግባል፤
9. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከተግባርና ሀላፊነቱ ውስጥ ከፊሉን አግባብ ላላቸው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

4. With the details to be determined by a directive, properly record and keep documents concerning rural land administration and use;
5. follow up whether or not land holders and users discharge the obligation legally entrusted upon them; and thereby take administrative measure on those who fail to discharge their obligations;
6. Review complaints of holders and users against preliminary administrative decisions given by kebele land administration and use committee; revise, approve and annul decisions of imprisonment;
7. Record and keep lands being under the government holding in the woreda; follow up their administration and management;
8. Record rent, mortgage, donation and similar agreements in relation to rural land during the time and on condition that there is no an established body to carry out such a duty in the woreda;
9. Wherever it finds it necessary, he may delegate part of his duties and responsibilities to appropriate land administration and use committees

## 26. ?? ?? ??????? ????? ?? ? ???? ??? ? ??????? ?? ?

1. የቀበሌና የንዑስ ቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ አባላት በየሶስት ዓመቱ በአካባቢው ነዋሪ ህዝብ ይመረጣሉ፣
2. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አባላቱ ለዳግመኛ ጊዜ ለአንድ ተጨማሪ የአገልግሎት ዘመን ሊመረጡ የሚችሉ ሲሆን ጥፋት የፈፀሙ እንደሆነ ግን ለህዝብ አቅርቦ በማስተቸት የአገልግሎት ዘመናቸው ከማብቃቱ በፊት ከሀላፊነታቸው እንዲነሱ ሊደረግ ይችላል።
3. የየኮሚቴ አባላቱ ቁጥርና አመራረጣቸው የሚካሔድበትም ሆነ ስራቸውን የሚያከናውኑበት ዝርዝር ሁኔታ ባለስልጣኑ ይህንን ደንብ ተከትሎ በሚያወጣው መመሪያ ይደነገጋል።
4. የቀበሌና የንዑስ ቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች ስለአከናወኗቸው ተግባራት በየ 6 ወሩ ለመረጣቸው ህዝብ ሪፖርት ያቀርባሉ፤ በተወካዮቻቸው አማካኝነት በዓመት አንድ ጊዜ የአሰራር ልምዳቸውን የሚለዋወጡበትንና በሌሎች የጋራ ጉዳዮቻቸው ላይ ተገናኝተው የሚመክሩበትን ወረዳ አቀፍ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጉባዔ ያካሔዳሉ። የጉባዔው አጠራርና አፈፃፀም ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

## 26. Selection and Term of Office of Land Administration and Use Committee members

1. The kebele and sub-kebele land administration and use committees shall be selected by local residing people every three-year;
2. Where it is found necessary, the members may be selected for second time of one additional term of office and provided, however, that where they commit offence, having presented them to the people and criticized, they may be disposed of from their responsibilities before the termination of their term of office;
3. Specific conditions of which each committee members' number and their selection may be undergone as well as they carry out their work shall be provided by a directive may be issued subsequent to this regulation,
4. The kebele and sub-kebele land administration and use committees shall submit to the people who selected them reports of activities they have carried out every six month. They hold woreda wide land administration and use conference which they have met and may exchange their working experiences and deliberated over other common matters through the agent of their representatives once year. Calling and implementation of the conference shall be determined by a directive may be issued by the Authority.

## 27. ?? ?? ??????? ????? ?? ??? ????? ?????

የቀበሌ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች ይህንን ደንብ በማስፈፀም ረገድ ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ተግባራትና ሀላፊነቶች ይኖሯቸዋል:-

1. የቀበሌውን መሬት በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ያስተዳድራሉ፣ በውስጡ የሚገኘውን ትርፍ መሬት መዝግበው ይይዛሉ፣ ከባለስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር አጠቃቀሙን ይወስናሉ፤
2. ከቀበሌው ነዋሪዎች፣ ከድርጅቶችና የገጠር መሬት ያገኙ ዘንድ በህግ ከተፈቀደላቸው ሌሎች ሰዎች የሚቀርቡላቸውን መሬት ነክ ጥያቄዎች ተቀብለው ቅደም ተከተል በማስያዝ ተገቢውን ምላሽ ይሰጣሉ፤
3. በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ የመሬት ባለይዞታዎችን ይመዘግባሉ፣ መረጃዎችን በጥንቃቄ ይይዛሉ፣ ይጠብቃሉ፤
4. በባለስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት በኩል የተመዘገቡ የመሬት ይዞታ፣ ኪራይ፣ ዋስትና ስጦታና የመሳሰሉትን ስምምነቶች ቅጅ ተቀብለው ይይዛሉ ይጠብቃሉ፣

## 27. Duties and Responsibilities of Land Administration and Use committees

The kebele land administration and use committees shall, in respect to implement this regulation, have specific duties and responsibilities indicated herein below:

1. Manage the kebele land, pursuant to the proclamation and this regulation hereof; record and keep unoccupied extra land found therein and determine its utilization in collaboration with the Authority's Woreda representative office.
2. Having received and arranged in order land-related requests may be submitted to them from kebele residents, organizations and other persons who are legally permitted with the view to acquiring rural land, give appropriate reply thereof;
3. Record land holders available in the kebele; carefully keep and save documents;
4. having received land holding, rent, mortgage, donation and similar copies of agreements registered through the Authority's woreda representative office, record and save same;

5. መሬታቸውን ባግባቡ ላልያዙ ተጠቃሚዎች የቃልና የመጀመሪያ ደረጃ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣሉ፣ በዚሁ ካልታረሙም ተከታዩ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስድባቸው ዘንድ ሁኔታውን ለሚመለከተው የባለስልጣኑ ወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት ሪፖርት ያደርጋሉ፤

6. በቀበሌው ውስጥ የሚገኙትን የወል ይዞታ መሬቶች አስተዳደርና ልማት በተመለከተ ከቀበሌ አስተዳደሮችና ከባለስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት ጋር በመመካከር ይወስናሉ።

7. የቀበሌው ነዋሪ ህዝብ በመሬት ነክ መብቶችና ግዴታዎች ዙሪያ በቂና ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማዳበሪያ ትምህርት የሚያገኝበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ፣ ይህንኑም ከባለስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት ጋር በመገናኘት ያስፈፅማሉ።

## 28. ???? ??? ? ?? ??????? ????? ?? ??? ????? ?????

የንዑስ ቀበሌ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች ይህንን ደንብ በማስፈፀም ረገድ የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነቶች ይኖራቸዋል:-

1. የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጉዳዮችን አስመልክቶ የንዑስ ቀበሌውን ኗሪ ህዝብ ይወክላሉ፣

5. Give oral and preliminary written warnings to those users who do not properly handle their land; unless they correct themselves in this warning, report it to the concerned Authority's woreda representative office with the view to be taken the next administrative measure on them;

6. Decide upon regarding administration and development of communal holding lands found in the kebele in consultation with kebele administrations and the Authority's of Woreda representative office.

7. Create favorable conditions through which the kebele resident people may get sufficient and continuing awareness raising education in relation to land related rights and obligations of the kebele resident people. Implement this in communicating with the Authority's Woreda representative office.

## 28. Duties and Responsibilities of sub-kebele Land Administration and Use Committees

The sub-kebele land administration and use committees shall, with respect to the implementation of this regulation, have the following duties and responsibilities:

1. represent the sub kebele residing people with regard to affairs of rural land administration and use;

2. የንዑስ ቀበሌው ኗሪ ህዝብ በመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጉዳዮች ረገድ ተገቢውን ግንዛቤ እንዲይዝ ያደርጋል፣
3. በንዑስ ቀበሌው ውስጥ የሚገኙትን የመሬት ተጠቃሚዎች ዝርዝር መዝግቦ ይይዛል፣ ለታቀፈበት የቀበሌ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ያስተላልፋል፣
4. አዳዲሰ የመሬት ይዞታ ጥያቄዎችን ያሰባስባል፣ ከንዑስ ቀበሌው ህዝቡ ጋር በመሆን ቅደም ተከተል እያስያዙ ለቀበሌው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ያቀርባል፣
5. መሬታቸውን በአግባቡ ላልያዙ ተጠቃሚዎች የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤ ተግባራዊ ሳያደርጉ በቀሩት ላይ ደግሞ ለቀበሌው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ሪፖርት ያደርጋል።

2. Cause the sub kebele residing people to have proper awareness with respect to land administration and use affairs;
3. Record and keep lists of land users found in the sub kebele and then transfer same to the kebele land administration and use committee to which it has been embraced;
4. Collect new land holding requests; arrange them in their order of time together with sub-kebele people and then submit same to the kebele land administration and use committee;
5. Provide an advisory service to those users who do not manage their land properly; report those who failed to put in practice the advice to the kebele land administration and use committee.

## ክፍል ሰባት

## የገጠር መሬት ይዞታ ለህዝብ አገልግሎት ስለሚለቀቅበትና ለንብረት ካሣ ስለሚከፈልበት ሁኔታ

### 29. ? ??? ???? ????? ? ??? ??? ????

1. የገጠር መሬትን ለህዝብ አገልግሎት ለማዋል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ባለስልጣኑ

## PART SEVEN

## CONDITIONS OF EXPROPRIATING RURAL LAND HOLDING FOR PUBLIC SERVICE AND DISBURSING OF COMPENSATION FOR PROPERTY

### 29. Expropriating Land for Public Service

**1.** Wherever the Authority finds it necessary to use rural land for public service, causing

በቅድሚያ ተመጣጣኝ የንብረት ካሣ በወቅቱ የገቢያ ዋጋ ግምት እንዲከፈለው በማድረግ የማንኛውንም ሰው ይዞታ ሊወስድ ወይም መሬቱን እንዲለቅ ሊወስን ይችላል።

2. መሬቱ የሚለቀቅበት ተግባር ከአካባቢው ህብረተሰብ ልማት ጋር በቀጥታ የተቆራኘ ሆኖ ሲገኝ ወይም ህብረተሰቡ ለሚለቀቀው መሬት ራሱ ካሣ ከፋይ በሚሆንበት ጊዜ ይኸው መሬት እንዲለቀቅ ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት ጉዳዩ መሬቱ ለሚገኝበት ቀበሌ ነዋሪ ህዝብ ቀርቦ አስተያየት እንዲሰጥበት መደረግና በአብዛኛው ህዝብ መደገፍ አለበት።

3. የገጠርን መሬት ለህዝብ አገልግሎት የማስለቀቅ ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል:-

ሀ/ የይለቀቅልኝ ጥያቄው ተፈላጊው መሬት የሚገኝበትን ቦታና የሚውልበት ተግባር በአዋጁ እንደተተረጎመው ከህዝብ አገልግሎት ጋር የተያያዘ መሆኑን ከሚያሣይ መግለጫ ጋር በመሬቱ ላይ የታቀደው ስራ ከመጀመሩ ቢያንስ አንድዓመትአስቀድሞ ለባለስልጣኑ ተጠሪ ጽ/ቤት መቅረብ ያለበት መሆኑ፤

ለ/ ጥያቄው ለቀረበበት ተግባር የበለጠ አመቺ የሆነ ሌላ መሬት በአካባቢው አለመኖሩ፤

beforehand to be paid for him reasonable property compensation depending on the estimation of current market cost, the Authority may take away or decide to be expropriated the land holding of any person.

**2.** Where it is found that the purpose of expropriating the land is directly interrelated with development of local community or where the community itself is being a payer of compensation for the land that may be expropriated, prior to a decision is given to be expropriated such a land, the issue shall, submitted to the kebele resident people in which the land is confined, be recommended for and supported by a majority vote.

**3.** Prior to any decision is given to expropriate rural land for public service, the prerequisites indicated herein below shall be satisfied:

A. where the request shall be submitted to the Authority representative office accompanying with the statement indicating the place where the required land is found and the task of its use is related to public service, as it is interpreted in the proclamation, ahead of one year that the proposed activity on the land is begun;

B. where there is no another land in the area which is more suitable for the task to which the request is submitted:

ሐ/ ሌላ አማራጭ ማግኘት የማይቻል መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር የመሬት ማስለቀቅ ጥያቄው በወላጅ አልባ ህፃናት፣ በአቅመ ደካሞች ወይም በሴቶች ይዞታ ላይ ሊቀርብም ሆነ ሊወሰን የማይችል መሆኑ፤

መ/ እንዲለቀቅ ጥያቄ የቀረበበት መሬት ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ ስለሁኔታው አስቀድሞ በፅሁፍ እንዲያውቅ ማስፈለጉ፤

ሠ/ በሊዝ ወይም በኪራይ የተሰጠ ከሆነ የውሉ ዘመን ከማብቃቱ በፊት በክልሉ መንግሥት የልማት ፕሮግራሞች አነሳሽነት ካልሆነ በስተቀር ከየትኛውም ወገን የሚቀርብ የመሬት ይለቀቅልኝ ጥያቄ ተቀባይነት የማያገኝ መሆኑ።

4. የመሬት ማስለቀቁን ውሣኔ የሰጠው የባለስልጣኑ ወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት ውሣኔውን በፅሁፍ ለወረዳው አስተዳደር ማሣወቅ አለበት። ውሣኔው የደረሰው የወረዳ አስተዳደርም መሬቱ የሚለቀቅበትን ጊዜና የተወሰነውን ካሣ መጠን ገልፆ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ለመሬቱ ባልይዞታ ወይም ተጠቃሚ የማስለቀቂያ ትዕዛዝ በፅሁፍ መስጠት ይኖርበታል። የዚሁ ማስለቀቂያ ትዕዛዝ ቅጅ ለባለስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት መላክ አለበት።

C. unless it is ascertained that it may not be possible to find another alternative, where the request of land expropriation may not to be submitted and decided up on the holdings of orphans, incapable disable persons or women;

D. Whereas it is necessary that a holder or user of the land to which a request is submitted to be expropriated is made to notify in writing the condition of expropriation of the land in advance.

E. whereas if the land is granted in lease or in rent prior to the termination of the contractual period of time, unless it is from the Regional State development programs initiative, a claim of expropriation of land which is submitted from any party shall not gain acceptance;

**4.** The Authority’s woreda representative office that has made a decision of land expropriation shall notify the decision in writing to the woreda administration. The woreda administration to which the decision is communicated shall, having stated the time of expropriating land and the amount of fixed compensation, give an expropriating instruction in written to the holder or user of the land based on a directive that may be issued for the implementation of this regulation. A copy of this expropriating instruction shall be sent to the Authority’s woreda representative office.

5. ጉዳዩ የሚመለከተው የመሬት ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ የመሬት ማስለቀቅ ጥያቄውን የሚቃወምበት ህጋዊ ምክንያት ቢኖረው ማስታወቂያው በፅሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ ውሣኔ ከሰጠው አካል ቀጥሎ ላለው ለባለስለጣኑ መ/ቤት አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል። የባለስልጣኑ መ/ቤት የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል።

## 30. ???? ?????

1. ለሕዝብ አገልግሎት ለማዋል መሬቱን በቋሚነት እንዲለቅ የሚገደድ ማንኛውም ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ የሚከፈለው ካሣ የሚከተሉትን ያጠቃልላል:-

ሀ. በመሬቱ ላይ ያፈራውና ባለበት ሁኔታ አንስቶ ሊወስደው የማይችለው ንብረት ዋጋ ግምት፣

ለ. በመሬቱ ላይ ለተደረገ ቋሚ መሻሻል ያወጣው ገንዘብና ሥራውን ለማከናዎን የፈሰሰው ጉልበት ዋጋ ግምት፣

ሐ. የመሬቱ ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ መሬቱን እንዲለቅ ከመደረጉ በፊት በነበሩት ዓመታት ያገኘውን አማካይ ዓመታዊ ገቢ መሰረት በማድረግ የሚሰላ የሰብል ዋጋ ግምት።

2. መሬቱን በቋሚነት ለሕዝብ አገልግሎት እንዲለቅ የሚደረግ የመሬት ባለይዞታ ይህንኑ እንዲለቅ ከመደረጉ በፊት በነበሩት አምስት ዓመታት ያገኘው አማካይ ዓመታዊ ገቢ በአሥር ተባዝቶ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1

**5.** Where a land holder or user who may concern the matter has legal ground of his rejecting the request of land expropriation, he may submit his complains to the Authority government office next to the body who has given the decision within 15 days from the date of his communication of the notice in writing. The decision may be given by the Authority government office shall be final.

## 30. Determination of Compensation

**1.** A compensation that may be paid to any holder or user who is forced to be permanently expropriated from his land or user for public service shall include the followings:

A. An estimate of cost of asset he has produced on his land and could not lift up and take away from the land;

B. An estimate of money he has spent on his land for permanent improvement made and cost of labor invested in order to undertake the activity;

C. An estimate of cost of crop calculated on the basis of average annual income he has obtained before the years that the land holder or user is made to expropriate his land;

**2.** Any land holder who is made to expropriate permanently his land for public service shall be paid a compensation of expropriation that an average annual income he has obtained in five years before he is made to expropriate this land

ስር ከተደነገገው ካሣ በተጨማሪ የመፈናቀያ ካሣ ይከፈለዋል።

3. የመሬት ይዞታው የተለቀቀው ወይም ተጠቃሚነቱ የተቋረጠው በጊዚያዊነት ከሆነ የሚከፈለው የመፈናቀያ ካሣ መሬቱ እንዲለቀቅ ከመደረጉ በፊት በነበሩት አምስት ዓመታት የተገኘው አማካይ ዓመታዊ ገቢ መሬቱ እስኪመለስ ድረስ ባለው ጊዜ ይከፈለ ዋል። ይሁን እንጂ አንድ መሬት በጊዚያዊነት ከአምስት ዓመት ለበለጠ ጊዜ እንዲለቀቅ ከተደረገ በቋሚነት እንደለቀቀ ይቆጠራል።

4. መሬቱ ለሕዝብ አገልግሎት ሲለቀቅ ከተለቀቀው መሬት ወደ ሌላ መሬት በመዛወር እንደገና ለሚተከልና ከቀድሞው ያልተለየ አገልግሎት መስጠት ለሚችል ንብረት ንብረቱን ለማንሻ፣ ለማጓጓዣና መልሶ ለመትከል የሚያስፈልገውን ወጪ የሚተካ ካሣ ለመሬት ባለይዞታው ወይም ተጠቃሚው ይከፈለዋል።

5. በቀበሌው የልማት ፍላጎት መሠረት መሬቱን እንዲለቅ የተደረገ ባለይዞታ በምትክነት ሊሰጠው የሚችለው በመጠኑም ሆነ በምርታማነቱ እንዲሁም ከመኖሪያ ቦታው ባለው ርቀት ተመጣጣኝና ተመሳሳይ መሬት የተገኘለት መሆኑን የባለሥልጣኑ ወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት ያረጋገጠ እንደሆነ ምትክ መሬቱ ተሰጥቶት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሠረት መሬቱ እንዲለቀቅ ከመደረጉ በፊት ካሣ እንዲከፈል ይደረጋል።

is multiplied by ten in addition to the compensation provided under sub. Art.1 of this Article hereof,

**3.** Where the land holding is expropriated or terminated his utilization temporarily, he shall be paid, until the period of time the land is returned, an average annual income of product obtained in five years before the land is made to be expropriated; provided, however, that where a plot of land is made to be expropriated temporarily for more than five years, it shall be regarded as he permanently expropriates.

**4.** Where the land is expropriated for public service, compensation that may recompense the necessary expenditure for lifting, transporting and replanting the property which may be replanted by transferring it from the expropriated land to another land and may render service not different from the previous one.

**5.** A holder who is made to expropriate his land, on the basis of the kebele development interest, where the Authority representative office of woreda ascertained that a plot of land that may be granted to him as a replacement and is roughly equivalent and similar to in its area, its fertility as well as its distance away from his residing area having been granted the substitute land to him, prior to the land is made to be expropriated, cause the payment of compensation to him in accordance with the provisions of sub. Art. 1(A) and sub. Art. 4 of

this Article hereof.

6. መንግሥት በሚያካሂደው የልማት ሥራ ለሕዝብ አገልግሎት የሚለቀቀው መሬት ለግል ባለሀብት በሊዝ የተሰጠና የሊዝ ዘመኑ ያላለቀ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣(ለ) እና ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሠረት ከሚከፈለው ካሣ በተጨማሪ በሊዝ ተቀባዩ ምርጫ ለቀረው ዘመን የሚጠቀምበት ተመጣጣኝ ምትክ መሬት ይሰጠዋል ወይም የቀረው የሊዝ ዘመን ክፍያ መጠን ተሰልቶ ይቀነስለታል ወይም ይመለስለታል።

7. በግል ወይም በጋራ የተያዘና በኪራይ የተሰጠ መሬት የኪራይ ዘመኑ ከማለቁ በፊት ለሕዝብ አገልግሎት ለማዋል እንዲለቀቅ ከተደረገ የመሬቱ ባለይዞታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2፣ 3 እና 4 በተደነገገው መሠረት መሬቱን እንዲለቅ ከመደረጉ በፊት ካሣ ይከፈለዋል። ካሣ የተከፈለው ባለይዞታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ለተከራዩ ካሣ የመክፈልና ላላለቀው የኪራይ ዘመን ክፍያውን አስልቶ የመቀነስ ወይም የመመለስ ግዴታ አለበት።

8. የካሣውን ጠቅላላ መጠን ለመወሰን የሚያስችለው ዝርዝር አሰራር በመመሪያ ይወሰናል።

**6.** Where the land that may be expropriated for public service in development activity undertaking by government is given to an investor in lease and its term of lease is not terminated, in addition to the compensation may be paid to him in accordance with the provisions of sub. Art. 1 (A), (B) and sub. Art. 4 of this Article hereof, the choice of the lessee, he shall be granted equivalent replacement land he may be used for the rest of term of the lease or the amount of payment of the rest lease term is calculated and then deducted or given back to him.

**7.** Where the land which is held in private or common and has been granted in lease is made to be expropriated so as to employ for public service, prior to he is made to expropriate his land the land holder shall be paid a compensation pursuant to the provisions of sub. Art. 1, 2, 3 and 4 of this Article hereof. The holder who is paid a compensation shall have an obligation to pay compensation for the lessee and, having calculated the payment of the rest term of rent deduct or give it back for him

**8.** specific working which may enable it to fix the general amount of compensation shall be determined by a directive

## 31. ???? ?????? ? ??? ?? ? ????

1. ለሕዝብ አገልግሎት መሬት እንዲለቀቅ በባለሥልጣኑ ከተወሰነ በኋላ የመሬት ርክክብ ከመደረጉ በፊት በዚህ ደንብ በተደነገገው መሰረት የተወሰነው ካሣ በሙሉ መከፈል አለበት፣

2. መሬቱን እንዲለቅ የተወሰነበት ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ ካሣውን ከተቀበለ በኋላ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሠረት በተገለፀለት የጊዜ ገደብ ውስጥ መሬቱን ለሚመለከተው ክፍል ማስረከብ አለበት፣

3. መሬቱን እንዲለቅ የተወሰነበት የመሬት ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ በተወሰነለት የካሣ መጠን ባለመስማማት ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ካሣውን አልቀበልም ያለ እንደሆን የባለሥልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት የሚከፈለውን ካሣ በራሱ ስም በዝግ የባንክ ሂሣብ በማስቀመጥ ገንዘቡን ያስቀመጠበትን ማስረጃ ቅጂ አያይዞ መሬቱ እንዲለቀቅለት በጽሑፍ የወረዳውን አስተዳደር ሊጠይቅ ይችላል። የወረዳው አስተዳደርም በቀረበለት ጥያቄ መሰረት የማስለቀቂያ ትዕዛዝ ይሰጣል።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ከወረዳው አስተዳደር የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የደረሰው ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ካሣ የተከፈለው የመሬት ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ፡-

## 31. Payment of Compensation and Handing Over of the Land

1. After it has been decided on that a land is to be expropriated for public service, prior to hand over land is made, the compensation which is determined in accordance with the provision of this regulation hereof shall be fully paid.

2. A holder or user to whom it is determined to expropriate his land shall, after he has received the compensation, hand his land over to concerned body within definite time stated to him in accordance with the provision of sub. At. 4 of this Article hereof.

3. Where a land holder or user to whom it is determined to expropriate his land refuses to accept the compensation due to his disagreement against the amount of compensation determined for him or any other reason, the Authority representative office of woreda shall, having put aside the money in its name in closed bank account and attached together with copy of evidence therewith, request the woreda administration in writing to be expropriated the land. The woreda administration shall give warning instruction based the request submitted to it.

4. Any land holder or user who has been paid compensation pursuant to sub. Art. 1 of this Article hereof, or given warning instruction from the woreda administration shall hand his land over within:

ሀ. በሚለቀቀው መሬት ላይ ሰብል፣ ቋሚ ተክል ወይም ሌላ ንብረት ካለ የመሬት ይለቀቅልኝ ማስታወቂያው በደረሰው በስልሳ ቀናት ውስጥ፣

ለ. በሚለቀቀው መሬት ላይ ሰብል፣ ቋሚ ተክል ወይም ሌላ ንብረት ከሌለ የመሬት ይለቀቅልኝ ማስታወቂያው በደረሰው በሰላሳ ቀናት ውስጥ መሬቱን ማስረከብ ይኖርበታል።

5. መሬቱን እንዲለቅ የተወሰነበት ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ካሣ ከተከፈለው ወይም በንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የመሬት ይለቀቅልኝ ትዕዛዝ ከደረሰው በኋላ መሬቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ሆኖ ያልተገኘ እንደሆነ የወረዳው አስተዳደር ያለተጨማሪ ሥነሥርዓት የሕግ አስከባሪ አካላትን አሰማርቶ መሬቱን ሊያስለቅቀው ይችላል።

## 32. ?????? ??? ? ?

1. በሚለቀቀው መሬት ላይ የሚገኘውን ንብረት ዋጋ ግምትና ሌላውን የካሣ መጠን ተምኖ መከፈል ያለበትን ጠቅላላ ካሣ የመወሰን ሥልጣን በዚህ ደንብ ለባለሥልጣኑ ተሰጥቷል።

2. ባለሥልጣኑ ካሉት የራሱ ባለሙያዎች እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች መካከል ከሶስት የማያንሱና ከአምስት የማይበልጡ አባላት ያሉበት ኮሚቴ በመሰየም፣ በተመሰከረለት የግል ወይም የመንግሥት

A. sixty days form the date he has communicated warning of land expropriating if there is crop, perennial plant or another asset on the lnad may be expropriated;

B. thirty days from the date he has communicated warning of land expropriating if there is no crop, perennial plant or another asset on the land may be expropriated.

**5.** Any holder or user to whom it is determined to expropriate his land after he has been paid compensation in accordance with sub. Art. 1 of this Article or land expropriating instruction is reached him, in accordance with sub. Art. 3 of this article, where he is not willing to hand his land over, the woreda administration shall, without additional procedure, having deployed law and order maintaining bodies; expropriate the land.

## 32. Property Assessment

**1.** The power of determining payable general compensation shall, having assessed the estimate of asset found on the expropriating land and other compensation, be vested to the Authority by this regulation hereof.

**2.** The Authority may cause the submission of general amount of payable compensation assessed pursuant to the provisions of this regulation hereof, by designating a committee of not less than three but not more than five

ተቋም አማካሪነት መከፈል የሚገባው ካሣ ጠቅላላ መጠን በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት ተገምቶ እንዲቀርብ ሊያደርግ ይችላል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም በሚለቀቀው መሬት ላይ የሚገኘውን ንብረት ለመገመት የተለየ እውቀትና ልምድ የሚጠይቅ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ባለሥልጣኑ የንብረት ገማቾችን በተለየ ሁኔታ ሊሰይምና ሊያስገምት ይችላል።

## 33. ??? ? ? ?? ????? ?? ???? ??? ???

1. በተወሰነው የካሣ መጠን ወይም በካሣው አከፋፈል ሁኔታ ቅር የተሰኘ የመሬት ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ በዚህ ደንብ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 4 ስር በተደነገገው መሠረት የማስለቀቂያ ትዕዛዝ ከደረሰው ቀን ቀጥሎ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለካሣ ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል።

2. ባለሥልጣኑ ከሦስት ያላነሱ፣ ከአምስት ያልበለጡ ባለሙያዎች በአባልነት ያሉበት የካሣ ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ያቋቁማል።

members comprising from its existing professionals as well as among government offices which concern the case with the advisory of certified private or government institution.

**3.** Notwithstanding the provision of sub. Art. 2 of this Article hereof, Where it is found that it requires special knowledge and experience to assess the property which is available on the expropriating land, the Authority may designate valuer of property in special condition and cause the assessment of same.

## 33. Submission of Complaints about fixing and payment of compensation

**1.** Any land holder or user who complains about the amount of fixed compensation or the conditions of compensation payment may, pursuant to the provisions of sub. Art. 4 of Art. 29 of this regulation hereof, lodge his complaint to compensation grievance review committee within thirty days form the date of his receipt of warning instruction.

**2.** The Authority shall establish compensation grievance review committee, not less than three, but not more than five members which comprise professionals thereon.

3. የካሣ ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴው ሥልጣን ባለጉዳዮችን በማነጋገር አቤቱታውን አጣርቶ በጉዳዩ ላይ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔ መስጠት ይሆናል።

4. ኮሚቴው የሰጠውን ውሳኔ ለአቤቱታ አቅራቢውና ለባለስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት በፅሁፍ ያሳውቃል።

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ስር በተደነገገው መሠረት የካሣ ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴው በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለከፍተኛው ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል።

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት በቀረበለት ይግባኝ ላይ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል።

7. በተወሰነው የካሣ መጠን ወይም በካሣው አከፋፈል ላይ ቅር በመሰኘት አቤቱታ ወይም ይግባኝ መቅረቡ ለሕዝብ አገልግሎት እንዲለቀቅ የተወሰነውን መሬት ርክክብ እንዲታገድ አያደርግውም።

## ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 34. ?? ??? ????

ማንኛውም የመሬት ድልድል፣ የይዞታ

3. The power of compensation grievance review committee shall, having communicated with the parties and reviewed the petition, be to give decision on the case within the period of limitation may be specified by a directive issued to implement this regulation.

4. The committee shall notify the decision it has given to the complainer and the Authority's woreda representative office in writing.

5. In accordance with the provision of sub. Art 4 of this Article hereof, any party who has been aggrieved by the decision of the compensation grievance review committee may submit his appeal to the high court within thirty days from the date of his communication of the decision.

6. In accordance with sub. Art. 5 of this Article hereof, the decision which the high court has given on the appeal submitted to it shall be final.

7. Submission of a petition or appeal being aggrieved at the amount of fixed compensation or compensation payment shall not cause to be suspended from handing over of the land determined to be expropriated for public service.

## PART EIGHT
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 34. Public Participation

Prior to any decision that may suspend or

ማረጋገጫ ደብተር አሰጣጥ፣ የወል መሬትን ለግል የማከፋፈል ውሳኔ፣ አንድን መሬት ከሌላ አገልግሎት ወደ የወል ተግባር የማዋል ውሳኔ፣ የገጠር መሬትን ለሕዝብ አገልግሎት ለማዋል ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም የመሬት ይዞታ መብት የሚያግድ ወይም የሚያሳጣ ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት የቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ እንዲወያይበትና ሃሣብ እንዲሰጥበት ይደረጋል። ለሥራው አመቺነትና ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት እንደሚያስችል ከታመነበት የዚህ ዓይነቱ ውይይት ባለይዞታው ለሚኖርበት ጎጥ ሕዝብ ብቻ ቀርቦ ውይይት ሊደረግበት ይችላል።

deprive of land holding rights is given, any land redistribution, granting of holding certificate book, decision of sharing out the communal land to private use, decision of making the use of plot of land for communal task from another service, unless the intension of rural land to use for public service, the kebele residing people shall be caused to deliberate and proposed over it. Such kind of deliberation may, having been submitted to only the village people that the holder resides, cause the deliberation over the case if it is believed in its capability to give fair decision and favorability for the work.

## 35. ??? ????? ??? ???? ? ??

1. ከመሬት ይዞታና ከመጠቀም መብት ጋር በተያያዘ የሚነሳ ማናቸውም ፍትሀብሔር ነክ አለመግባባት በመጀመሪያ ደረጃ በባለጉዳዮች ፈቃድ በስምምነት እንዲፈታ ጥረት መደረግ አለበት። በመሬት ባለይዞታዎች ወይም ተጠቃሚዎች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በስምምነት የመፍታቱን አሠራር ተግባራዊ ለማድረግ የቀበሌው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ከየንዑስ ቀበሌው የተውጣጡ አባላት የሚገኙበት የአካባቢ ሽማግሌዎች ሸንጐ በየሚመለከታቸው ማህበረሰቦች ምርጫ ያቋቁማል።
2. የሽማግሌዎቹ አመራረጥና የእርቁ ድርድር አካሄድ በየአካባቢው ባህል መሠረት ይፈፀማል።

## 35. Conditions of Resolving Disputes

1. Any civil code dispute arising in related to land holding and use rights, first of all, shall be made every endeavor to be resolved on the base of consent of parties. In order to put in place the working of resolving disputes in agreement which may be happened among land holders or users, local arbitrators assembly whose members are comprising from each sub-kebele of the kebele land administration and use committee shall be established.
2. The selection of arbitrators and negotiating bargaining process of the reconciliation shall be executed on the basis of customary of each

surrounding.

3. በባለጉዳዮች ስምምነት ላይ ተመስርቶ የሽማግሌዎች ሸንጐ በፈታው አለመግባባት ላይ አዲስ የፍትሐብሔር ክስም ሆነ ይግባኝ ሊቀርብበት አይችልም።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ስር የተደነገገው ቢኖርም አለመግባባቱ በዚህ ደረጃ ሊፈታ ያልቻለ እንደሆነ በስምምነት የመፍታቱ ጥረት ከተቋረጠበት ቀን ቀጥሎ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው ወረዳ ፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይቻላል።

**3.** A new civil charge as well as an appeal shall not be brought on the disputes resolved by arbitrary assembly on the basis of agreement of the parties.

**4.** Notwithstanding the provision under sub. Art. 3 of this Article hereof, Where the dispute is not resolved at this level, it may be possible to bring a petition to the respective woreda court within thirty days from the date of termination of resolving effort in agreement.

## 36. ???????? ????? ?? ??? ??? ????

1. በመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች ውሣኔላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ ውሣኔው በተሰጠ በ15 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን በማስረጃ ደግፎ አግባብ ላለው የባለስልጣኑ ወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤትሊያመለክትና ሊያስመረምር ይችላል።
2. የዚህ ደንብ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ 5 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የባለስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ውሣኔው በደረሰው በሰላሣ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለወረዳ ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል።
3. የወረዳው ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ

## 36. Submission of Appeal Against Administrative Decisions

**1.** Any rural land holder or user who is aggrieved at the decision of land administration and use committees may appeal his petition, by supporting it with evidence, to the respective Authority of representative office of woreda and may get reviewed thereof.

**2.** Without prejudice to the provision of sub. Art. 5 of At. 33 of this regulation hereof, any party who is aggrieved at the decision made by the Authority of representative office of woreda may submit his appeal to woreda court within thirty days from the date of his communicating the decision.

**3.** Any party who is aggrieved at the decision of

ወገን አግባብ ባለው ህግ መሠረት እንደተገቢነቱ ይግባኙን ወይም የሰበር አቤቱታውን ለከፍተኛው ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል።

## 37. ??? ?? ???? ???? ??

1. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም የገጠር መሬት ይዞታንና አጠቃቀምን በተመለከተ በመሬት ባለይዞታዎች ወይም በተጠቃሚዎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በአካባቢው ባሕላዊ ደንቦች መሠረት እንዲፈቱ የቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ በመወያየት ወስኖ ይኸው በጽሁፍ እንዲቀመጥ ማድረጉ የታወቀ እንደሆነ ማናቸውም አይነት አለመግባባት በእነዚሁ ባህላዊ ደንቦች እንዲፈታ ይደረጋል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም ባሕላዊ ደንቦቹ አግባብ ካላቸው የክልልና የፌዴራል ሕጎች ጋር የሚቃረኑ ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

## 38. ??? ??? ?

መሬቱን በመንከባከብ፣ በማልማት፣ በእቅዱ መሠረት በመጠቀም፣ አካባቢውን በመጠበቅ፣ ለአካባቢው ጠቃሚና ተስማሚ የሆኑ ዛፎችን በመትከልና በማሳደግ፣ በመስኖ አጠቃቀም፣ በእርሻ አስተራረስ፣ በእንሰሳት አረባብ ዘዴ እና በመሳሰሉት አርአያ የሚሆን ተግባር ላከናወኑ የመሬት ባለይዞታዎች ወይም ተጠቃሚዎች የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት አቅሙ በፈቀደ መጠን የማበረታቻ ሽልማት ይሰጣል። ዝርዝሩ ይህንኑ ደንብ ተከትሎ

the woreda court shall, in accordance with appropriate law, as it may be proper, submit his appeal or his broken petition to the high court.

## 37. Application of Customary Rules

1. Notwithstanding the provision stipulated under sub. Art. 1 of Art. 35 herein above, where it is known that the kebele residing people, having decided by deliberating over the issue disputes that may arise among land holders or users, with regard to rural land holding and use, to be resolved based on the customary rules of the surrounding and made such a rule to be kept in writing, it shall be caused any dispute to be resolved on the basis of these customary rules.
2. Notwithstanding the provision stipulated under sub. Art. 1 of this Article hereof, if the customary rules come into conflict with the proper laws of the Region and Federal, they shall not be applicable.

## 38. Incentives

The Authority government office shall, to the extent its capacity permits, grant encouraging reward to those land holders or users who have performed exemplary task of taking care of, developing, using on the basis of plan of his land, protecting his surrounding, planting and growing trees which are useful and suitable for the surrounding, in irrigation utilization, in plowing up fields, in animal husbandry method

በሚያወጣ መመሪያ ይወሰናል።

and similar ones. Particulars shall be determined by a directive may be issued following this regulation.

## 39. ???? ? ?? ? ? ??? ?? ?? ? ???? ?? ??? ??? ??? ????

ይህ ደንብ ከመፅናቱ በፊት በቀደምት ህጐች የተመሰረቱና ከገጠር መሬት ይዞታም ሆነ አጠቃቀም ጋር ተያያዥነት ያላቸው መብቶችና ግዴታዎች የዚህን ደንብ መሠረታዊ ድንጋጌዎች እስካልተቃረኑ ድረስ ባቋቋሚቸው ህጐች መሠረት ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል።

## 39. Effectiveness of Rights and obligations sourced from previous laws

Rights and obligations connected with rural land holding and use which are established under former laws before the coming into force of this regulation shall continue their application in accordance with their established laws unless they come into conflict the fundamental provisions of this regulation therein.

## 40. ?? ???? ???? ????? ?????

1. ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ በማስፈፀም ረገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት።
2. የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የጣሰ ወይም አፈፃፀማቸውን ያሰናከለ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

## 40. Collaboration Obligation and Criminal Responsibility

1. Any person shall have an obligation to cooperate with concerned bodies with respect to implementing this regulation
2. Any person who violates or obstructs the execution of this regulation shall be accountable in accordance with provisions of criminal law.

## 41. ???? ?? ???????? ???

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ሌላ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 41. Inapplicable Laws

Any other regulation, directive, customary practice which contradicts this regulation may not apply with regard to matters provided for therein.

## 42. ? ? ?? ?? ? ? ? ? ? ? ?

ባለሥልጣኑ ይህንን ደንብ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

## 43. ??? ?? ???? ??

ይህ ደንብ ለክልሉ መንግሥት ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባሕር ዳር
ግንቦት 3 ቀን 1999 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልል
መስተዳድር ምክር ቤት

## 42. Power to Issue Directive

The Authority may issue directives necessary in order to fully implement this regulation.

## 43. Effective Date

This regulation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre-Hig Gazette of the Regional State

Done at Bahir Dar,
This 11th day of May, 2007
Council of the Amhara National
Regional Government